Berhan International Research Journal of Science and Humanities
(BIRJSH), 2026, 10(1), 64-79

*Journal homepage*: www.journals.dbu.et *ISSN: 2414-2794, eISSN: 3006-578X*

# A Moral-Philosophical Analysis of Selected Novels by Sibhat Gebre-Egziabher and Be'alu Girma

**Dessalegn Seyoum Feleke [1], Ayele Fikre[1], Fasil Merawe Tessagaye[2]**

[1] Addis Ababa University, College of Education and Behavioral Studies, Department of Amharic Language, Literature and FolkLore.
2 Addis Ababa University, College Social Science, Arts and Humanities, Department of Philosophy.

*DOI: https://doi.org/10.61593/DBU.BIRJSH.01.10.05*

**Abstract**

The contemporary period is marked by the persistent emergence of moral questions that shape everyday human conduct. From the moment individuals leave their homes until they reach their workplaces, educational institutions, or places of worship, they engage in actions that raise fundamental concerns of moral philosophy. During these activities, individuals evaluate values, exercise moral judgment, and confront ethical dilemmas that require decision-making or deliberate restraint. Consequently, moral philosophy has attracted increasing scholarly attention. Literature constitutes one of the principal artistic domains through which moral philosophy is articulated, interrogated, and critically examined. Although Sibhat Gebre-Egziabher and Be'alu Girma were contemporaries and maintained a close personal relationship, no prior scholarly study has been identified that systematically examines their works in parallel with a view to analyzing their moral perspectives. This absence of comparative analysis provides the primary impetus for the present study. The study examines four purposively selected novels—The Sebategnaw melak (Seventh Angel) and Tikusat (Heat) by Sibhat Gebre-Egziabher, and Yehilina Dwol (Conscience Bell) and Hadis by Be'alu Girma. Its central objective is to analyze the moral ideas articulated in these works within the framework of normative (prescriptive) ethics. The findings of the study reveal that the two authors adopt fundamentally contrasting moral orientations. Sibhat Gebre-Egziabher's novels reflect an ethical egoist perspective that prioritizes individual happiness and self-interest. In contrast, Be'alu Girma's novels articulate an altruistic moral framework that emphasizes individual self-sacrifice as a means of securing the well-being and happiness of the broader community.

**Keywords:** normative ethics, altruism, egoism

*Corresponding author email: Dessalegn.seyoum@aau.edu.et or desephilo@gmail.com
Article information: Received 10 September 2025; Revised on 01 February 2026; Accepted on 05 April 2026

**© 2026 Debre Berhan University. All rights reserved.**

**የግብረ ገብ ፍልስፍና  በተመረጡ የሥብሐት ገብረ እግዚአብሔርና በዓሉ ግርማ ልቦለዶች ውስጥ**

**አጠቃሎ**

ይህ ያለንበት ዘመን በርካታ  የምግባር ጥያቄዎች የሚነሱበት ነው። ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው መሥሪያ ቦታቸው ወይም ትምህርት ቤት ወይም የእምነት ሥፍራ እስኪደርሱ  የነገረ ግብረ ገብ (Moral Philosophy) ጉዳይ የሚሆኑ ተግባራትን ይከውናሉ፣ ሐሳቦችን ያውጠነጥናሉ፣ ውሳኔዎችን ይወስናሉ ወይም በመወሰንና ባለመወሰን መኻል ይዋልላሉ። በሌላ በኩል ግብረ ገብ የአንድ ዘመንና የአንድ ጉዳይ ተጽዕኖ ውጤት አይደለም። የሃይማኖትና የባህል፣ የቤተሰብና የኪነ ጥበብ ወዘተ. ተጽዕኖዎች ድምር ውጤት ከመሆኑም በላይ ትናንት በዛሬ ላይ ፣ ዛሬ በነገ ነገረ ግብረ ገብ ላይ አስተዋጽኦም ተጽዕኖም ይኖረዋል። በዚህ ምክንያት ነገረ ግብረ

ገብ (የግብረ ገብ ፍልስፍና) የአጥኝዎችን ትኩረት ይበልጥ እየሳበ መጥቷል። ነገረ ግብረ ገብ ከሚገለጽባቸው፣ ከሚፈከርባቸው፣ ከሚተነተንባቸው ኪናዊ ሥራዎች ሥነ ጽሑፍ አንዱ ነው። በሌላ በኩል ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርና በዓሉ ግርማ የዘመን አቻዎችና ወዳጅነት የነበራቸው ደራስያን ቢሆኑም የሁለቱን ደራሲዎች ሥራ ጎን ለጎን በማናበብ የግብረ ገብ እይታዎቻቸውን ለመፈከር የተሠራ ጥናታዊ ሥራ አለመገኘቱ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። ለጥናቱ የተመረጡት አራት መጻሕፍት ማለትም ሰባተኛው መልአክና ትኩሳት በስብሐት ገብረ እግዚአብሔር እንዲሁም የህሊና ደወልና ሀዲስ በበዓሉ ግርማ ዓላማ መር በሆነ መረጣ ተመርጠዋል። በተመረጡትም ልበለዶች ውስጥ ደራሲዎቹ ምን ዓይነት የግብረ ገብ ፍልስፍናዎችን እንዳነሱ መተንተን የዚህ ጥናት ዓላማ ሲሆን የተመረጠው ጽንሰ ሐሳብም የእለት (መመሪያዊ) የምግባር ፍልስፍና (Normative Ethics) ነው። በዚህ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻለው ሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር እኔያዊ የምግባር ፍልስፍና (Ethical Egoism) ያንጸባረቀ ሲሆን በዓሉ ግርማ ተቃራኒ የሆነውን የመስዋዕትነት ምግባር ፍልስፍና (Altruistic Morality) ያንጸባርቃል። የሥብሐት ሥራዎች የግለሰብ ደስታና ጥቅምን ያማከሉ ሲሆኑ የበዓሉ ሥራዎች ግን በግለሰብ መስዋዕትነት የብዙኃንን ደስታና ጥቅም ማስጠበቅ ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው ተገኝተዋል።

**ቁልፍ ቃላት፡** የእለት (መምሪያዊ) ምግባር፣ መስዋዕትነት፣ እኔያዊነት

## አንድ፡ መግቢያ

ሥነ ጽሑፍ የእኔ የሚለው ጉዳይ አለው፤ ጉዳዩ እንደየደራሲው የሚመረጥ፣ የሚወሰንና የሚተገበር ቢሆንም ቅሉ። ይህ ‹‹ጉዳይ›› ከማኅበረሰቡ ወይም ለማኅበረሰቡ የሚሆን ነው። ሥነ ጽሑፍ የነበረውን ወይም የሆነውን፣ የሚኖረውን ወይም የሚሆነውን፣ ሊኖር የሚገባውን ወይም ሊሆን የሚገባውን፣ ሊኖር የሚገባውን ወይም ሊኖር የማይገባውን ‹‹ጉዳይ›› ‹‹ጉዳዬ›› ብሎ ያጠነጥናል። ደራሲ የራሱን ዕይታ፣ ያራሱን ዓለም አረዳድ፣ የራሱን የሐሳብ ፍሰት መንገድ ለመጠቀም ነጻነት ያለው ቢሆንም ራሱ ደራሲው የማኅበረሰብ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ነው። ደረቅ ፍልስፍናን ሳይሆን ፍልስፍናዊ ልበለዶችን በመጻፍ የሚታወቀው F. Nietzsche ስለዚህ ይመስላል እንዲህ የሚለው። ‹‹Very early in my life I took the question of the relation of art to truth seriously: even now I stand in holey dread in the face of this discordance›› (Quoted in J.M Bernstein 1992:1).

ከወጣኒነቴ ጀምሮ ራሴን የምጠይቀው ጥብቅ ጥያቄ በጥበብና በእውነት መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። ዛሬም ላይ ሆኜ እንኳ ለጥያቄው ያለኝ ምላሽ ወላዋይነት ነው እያለ ነው። ደራሲው የሚጽፈው የሰራውን ማኅበረሰብ ለመግለጽ ወይም በሠራው ማኅበረሰብ ላይ ለማመጽ ነው። እውነቱ እንዲህ ስለሆነ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ማኅበረሰብን እናያለን። በአንድ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ ማኅበረሰቡን ወይም ማኅበረሰባዊ እውነታዎችን እናያለን ስንል ግን ነገሩ የፍካሬ እንጅ ጥሬ ሀቅ የመቁጠር አይደለም። ሥነ ጽሑፉን በመፈከር እውነቱን መመርመር ካልሆነ በቀር እንደ ቀመር ሳይንስ (Natural Science) የሚለካ፣ የሚመዘን፣ የሚበየን፣ የሚዳኝ እውነት በቀጥታ እናገኛለን ማለት አይደለም። Bernstein የፍልስፍናን እና የሥነ ጽሑፍ ሙያዎችን በመረመሩበት ‹‹The Fate of Art›› በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ።

If art is taken as lying outside truth and reason then if art speakes in its own voice it does not speak truthfully or rationally; while if one defends art from within the confines of the language of truth-only cognition one belies the claim that art is more truthful than the truth only cognition (1992:2).

በዚህ መንገድ የብዙኃኑ ሆነ የነጠላው፣ የብርቱው ሆነ የደካማው፣ የቅርቡ ሆነ የሩቁ እውነታ የበለጠ ቅርብ፣ የበለጠ ስሉጥ፣ የበለጠ ግልጥ፣ የበለጠ ስፉህ፣ የበለጠ ጠሊቅ ሆኖ ይገለጻል፡፡ Bernstein ከላይ በተጠቀሰው የ F. Nietzsche ሐሳብ ላይ የሚከተለውን ያክላሉ፡፡

For Nietzsche but not for him alone, the discordance between art and truth arouses dread because art and aesthetics […] appear as somehow more truthfull than empirical truth […] more rational than methodical reason, more just than the liberal justice […] more valuable than prinicipled morality or utility. (1992:1-2)

Bernstein እንደሚሉት ጥበብ (ከጥበባት አንዱ ሥነ ጽሑፍ ነው) ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከሚደረስበት እውነት በላይ የላቀ እውነትን ይገልጻል፣ በሳይንሳዊ መንገድ ከሚሠራው አመክንዮ በላይ የሰውን አእምሮ ይቆጣጠራል ወይም ይፈታተናል፡፡ በመርህ ከሚታወቅ ህግ ወይም መመሪያ በላይ የግብረ ገብ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ሥነ ጽሑፍ ማኅበረሰቡን ጠልቆ ወይም መጥቆ አስፍቶ ወይም አጥብቦ የሚያይበት ብልሃት ስላለው ነው፡፡ ማኅበረሰብ ደግሞ ቅሩብ እውነት ሳይሆን ከምናዬው ነገር ባሻገር ያለ ዲበ አካላዊ እውነት ነው፡፡ ማኅበረሰብን ዲበ አካል የሚያደርገው የማኅበረሰቡ አባል የሆኑ ግለሰቦችን ማዬትና መለዬት ስለማይቻል ሳይሆን አባላቱን ያስተሳሰራቸውን እምነት፣ ርእይና ግብረ ገብ (ሞራል) ማዬትና መዳሰስ ስለማይቻል ነው፡፡ ሥነ ጽሑፍ ለኅብረተሰብ ወይም ከኅብረተሰብ በመሆኑ በአንድ ወይም በብዙ መንገድ ሥነ ጽሑፍ ርዕይን፣ እምነትን ወይም ግብረ ገብን ጉዳዩ ያደርጋል፡፡

ይህ ጥናት ሥነ ጽሑፍን ከፍልስፍና ጋር እያማጠቀ ለማጥናት የሚሞክር ነው፡፡ ነገረ ግብረ ገብ የሥነ ጽሑፍ ተግባር ነው ስንል ግን የሥነ ጽሑፍ ግብሩ ‹‹ሰባኪነት›› ነው ወደ ሚል ቁንጽል ምልከታ የሚወርድ አይደለም፡፡ ሥነ ጽሑፍ ነገረ ግብረ ገብን ጉዳዬ ብሎ ሲነሣ መስበክን ብቻ የመጨረሻ ግቡ አድርጎ አይደለም፡፡ ይልቁንም ራሱ ግብረ ገብ ምን እንደሆነ ለመፈከር፣ ለመመርመር እና ለመተንተንም ጭምር እንጅ፡፡ ስለዚህ ነገረ ግብረ ገብን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ማሰስ እዚህ ጋ ይበቃል ሊባል የማይችል ነገር ነው፡፡

ጠና ደዎ ‹‹በጎም ሆነ መጥፎ ድርጊት የሚፈጸመው በሰው ነው፡፡ የሚፈጸመውም በሰው ወይም ከሰው ጥቅም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ነገሮች ላይ ነው›› (2008፡2) እንዲሉ ሰውን ማዕከል የሚያደርጉ ሁሉ ነገረ ግብረ ገብ ጉዳያቸው ይሆናል፡፡ የተመረጡት ደራስያንና ሥራዎቻቸው ለጥናት መድረኩ አዲስ አይደሉም፡፡ በርካታ አጥኝዎች በተለያዬ ጉዳይ ጥናት እንደሠሩባቸው፤ በሁለቱም ደራስያን ህይወትና ሥራዎችም ላይ መጻሕፍት እንደ ተጻፈ ይታወቃል፡፡ (ዓለማየሑ ገላጋይ፡ ‹‹ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት (2000)፣ ዘነበ ወላ ‹‹ማስታወሻ›› (1997)፣ እንዳለጌታ ከበደ ‹‹በዓሉ ግርማ ሕይወቱና ሥራዎቹ (2008) ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው) ነገር ግን በደራስያኑም ሆነ በሥራዎቻቸው ላይ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት የተደረገው ከዚህ ጥናት ጋር በሚኖራቸው ዝምድና ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአማርኛ ልቦለዶችን ከነገረ ግብረ ገብ አንጻር ያጠኑ ጥናቶች እንዳሉ ፍለጋ አካሂጃለሁ፡፡ በተጨማሪም ከእኔ ጥናት ጋር የተዛመደ ጭብጥ ያላቸውን መጽሐፎች ለመቃኜት ተሞክሯል፡፡ ዝምድና ያላቸውን ጽሑፎች በሁለት ከፍሎ ማዬት የሚቻል ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ፍልስፍናን መሠረት አድርገው ሀገርኛ ምልከታን የሚያሳዩ መጻሕፍት እና ጉዳያቸውን የግብረ ገብ ፍልስፍና ላይ አድርገው በአማርኛ መጻሕፍት ላይ የተሠሩ ጥናቶች፡፡  ይህ ሲባል በኢትዮጵያ ውስጥ ሥነ ምግባርን ለማስተማር የተጻፉ መጻሕፍት የሉም ወይም ጥቂት ናቸው የሚል ምልከታ የለኝም፡፡ ተረትና ምሳሌ ከበደ ሚካኤል፣ ፍኖተ አእምሮ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ወዳጄ ልቤ ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣ ተረት ተረት የመሠረት ሀዲስ ዓለማዬሁ ሌሎችም በርካታ መጻሕፍትን እያነሡ ስለ ሥነ ምግባር የተጻፉ አይደሉምን? ማለት ይቻላል፡፡ የእኔ የጥናት ትኩረት ግን የሥነ ምግባር አስተምህሮዎችን (ሰበካዎችን) የሚመለከት ሳይሆን የምግባር ፍልስፍናን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የሚሰብኩትን ሳይሆን የሚበይኑትን የሚመርጥ ነው፡፡

ከላይ ባስቀመጥሁት መሥፈርት የተገኙት ተዛማጅ ጽሑፎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በመጻሕፍት በኩል የማነ ገብረ ማርያም (1996) የፍልስፍና መግቢያ ቅጽ 1፣  ጠና ደዎ (2008) ሰው፣ ግብረ ገብና ሥነ ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፣   ብሩህ ዓለም ነህ (2009) የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ ኤልያስ አያልነህ (2000) ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖብል፣  ደሳለኝ ሥዩም (2014) የፍልስፍና መግቢያ፡ መነሻው፣ ምንነቱ እና የጥናት መስኮቹ የተሰኙ መጻሕፍት ሲሆኑ እነዚህ መጻሕፍት የግብረ ገብ ፍልስፍናን የተማከለ ሐሳብ ይዘው የተገኙ ቢሆኑም አንዳቸውም እንኳ ሥነ ጽሑፋዊ ትንታኔ ያቀረቡ አይደሉም ወይም ሥነ ጽሑፍን አማክለው የተሰሩ አይደሉም፡፡፡ ከጥናታዊ ጽሑፎች ደግሞ የ Tena Shale. (2008) “The changing face of moral vision in Amharic novel” የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ እና የሰላማዊት በየነ (2010) ‹‹የተፈጥሮና የባህል ግጭትና ዕርቅ በ አዳም ረታ ህማማትና በገና ውስጥ›› የማስትሬት ዲግሪ ማሟያ

የተገኙ ቢሆኑም ግብረ ገብን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ተመለከቱ እንጅ ነገረ ግብረ ገብን (የግብረ ገብ ፍልስፍና)ን ይዘው አልተሠሩም። ይህ ጥናት ይሄንን የእውቀት ክፍተት ይሞላል።

ጥናቱ የግብረ ገብ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ነው ሲባል ግን በጠቅላላው የግብረ ገብ ፍልስፍናን ይቃኛል ማለት አይደለም። በመሠረቱ የግብረ ገብ እሳቤዎች (Moral Philosophy) በሦስት ታላላቅ መደብ ላይ የሚያርፉ ናቸው። የመጀመሪያው ረቂቅ የግብረ ገብ ጉዳዮች (Meta ethics) የግብረ ገብን ምንነት መፈተት ላይ የሚያተኩር ነው። ሁለተኛው መደብ የተፈቀዱ እና ያልተፈቀዱ፣ መጥፎና መልካም፣ ትክክልና ስህተት እያሉ የመበዬን ምልከታዎች ላይ የሚያተኩረው የእሴት (መመሪያዊ) ምግባር (Normative Ethics) ነው። ሦስተኛው ደግሞ ተግባራዊ በሆኑ የሕይወት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚመጡ አዳዲስ ሙያዊ ጉዳዮች ላይ የብያኔ ሥራን ለመሥራት የሚሞክረው ተግባራዊ ምግባር (Applied Ethics) ነው (ጠና፣ 2008:23፣33፣38)። የዚህ ጥናት ወሰን የእሴት (መመሪያዊ) ምግባር (Normative Ethics) ጽንሰ ሐሳባዊ ማህቀፍ አድርጎ የተመረጡትን መጽሐፎች መተንተን ነው።

ልቦለዶቹ በተመረጠው የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፍ ለማዬት፣ የይዘት ትንተና ለማድረግ በአንድ ጉዳይ ሥር ሊነበቡና ሊናበቡ የሚችሉ መሆናቸውን በመለዬት ዓላማ መር የሆነ የናሙና መረጣ ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ናቸው። የየደራሲዎቹን የግብረ ገብ ፍልስፍናዎች ለማግኘት ያመቻሉ በሚል አመክንዮ ከአንድ ደራሲ ሁለት ሥራዎች ተመርጠዋል። የተመረጡትም የስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሰባተኛው መልአክ እና ትኩሳት (ሁለቱም እንደወረደ እትሞች ናቸው)፣ እንዲሁም የበዓሉ ግርማ የህሊና ደወል እና ሀዲስ ናቸው። እነዚህ አራት መጻሕፍት የየደራሲዎቹ ተናባቢ ወይም ተሰናሳይ መጽሐፎች ናቸው። አስቀድሞ የታተመው የስብሐት ‹‹ሰባተኛው መልአክ›› (እንደረወደ) ደራሲው በፈረንሳይ ሀገር ተማሪ በነበረበት ዘመን ያሳለፈውን የወጣትነት ሕይወት ይተርካል፤ ቀጥሎ የተታተመው ‹‹ትኩሳት››ም ይሄንኑ የወጣትነት ትኩሳት ዘመን ይበልጥ አስፋፍቶ ይተርካል። የበዓሉ ግርማ ‹‹የህሊና ደወል›› አስቀድሞ የታተመ መጽሐፍ ነው፤ እንደገና ከዓመታት በኋላ ‹‹ሀዲስ›› ተብሎ ተስፋፍቶ ታትሟል። እነዚህ የየደራሲዎቹ ሁለት ሁለት መጻሕፍት ከትልም አንጻር ልዩነት የሌላቸው በመሆቸው ደራሲዎቹ የተከተሉትን የግብረ ገብ ፍልስፍና ይበልጥ አብራርተው ያሳያሉ በሚል አመክንዮ ለዚህ ትንታኔ ተመርጠዋል።

## ሁለት፡ ነገረ ግብረ ገብ (Moral Philosophy)

ነገረ ግብረ ገብ አንዱ የፍልስፍና ዘርፍ ነው። ይህም የፍልስፍና ዘርፍ ምግባርን እንደ አንድ የፍልስፍና የጥናት መስክ ያጠናል። አጠናኑም የፍልስፍና ሁነኛ መሣሪያ የሆነውን አመክንዮዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ሲሆን የግብረ ገብ (Moral) መርሆዎችን የሚያጠይቅ ዘርፍ ነው። Lewis Vaughn ‘Ethics: ‘Doing ethics: Moral reasoning and contemporary issues ’ በተሰኜ መጽሐፉ ‘Ethics is the philosophical study of morality – a rational examination of people’s behavior’ (2016:30) ይላል። ምግባር የግብረ ገብ ፍልስፍናዊ ጥናት ነው። የሰዎችን ግብረ ገብ በአመክንዮ ይመረምራል። ትክክልና ስህተት፣ መልካምና እኩይ ለሚሏቸው ጠባያትና ድርጊቶች መሠረት የሆኗቸውን መርሖዎች ያጠናል። የግብረ ገብ እሴቶችን ምንነት ይመረምራል። ለራሳችን እልፍ ሲልም ለሌሎች ያለብንን ኃላፊነቶች ይጠይቃል። ነገረ ግብረ ገብ ወይም የምግባር ጥናት ሰፊ የፍልስፍና ዘርፍ ከመሆኑ አንጻር በተለያዩ ንዑሳን ዘርፎች ተከፋፍሎ ይታያል።

ንዑሳን ዘርፎቹ የሚለያዩት ከሚያተኩሩበት ገጽታ፣ ከዘይቤና ዓላማቸው አኳያ ነው። እያንዳንዳቸው የተወሰነን የግብረ ገብ ጽንሰ ሐሳብ፣ ተግባርና አመክንዮ ገጾች ያመለክቱናል። እነዚህ ንዑሳን ዘርፎች በዋናነት ረቂቅ (ዲበ) ምግባር ፍልስፍና (Meta Ethics)፣ ተግባራዊ ፍልስፍና (Applied Ethics) እና የእሴት (መመሪያዊ) (Normative Ethics) ፍልስፍና ተብለው የሚገለጹ ናቸው። ይህ ጥናት ማህቀፍ የሚያደርገው የዕሴት (መመሪያዊ) የምግባር ፍልስፍናን በመሆኑ በዝርዝር እንየው።

### የዕሴት (መመሪያዊ) ምግባር (Normative Ethics)

የዕሴት ወይም መመሪያዊ ምግባር አንዱና ዋነኛው የግብረ ገብ ፍልስፍና ሲሆን የግብረ ገብ ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ የሆነውን ‹‹ሰዎች ምን ማድረግ አለባቸው?›› የሚል ጥያቄ የሚያነሣ፣ ሥርዓታዊ የሆነ የድርጊት ማህቀፍን ለማነጽ የሚሞክር የፍልስፍና ዘርፍ ነው።

ስለዚህም ዋነኛ ትኩረቱ ትክክል የሆነውን ስህተት ከሆነው የምንለይባቸውን የግብረ ገብ መርሖዎች (Moral Priniciples) መለየትና መሞገት ነው። (William 1973:2) እንደሚለው የዕሴት ወይም መመሪያዊ ምግባር ፍልስፍና የግብረ ገብ ብያኔዎችን ይዞት የሚመለከት ሲሆን ልክና ስህተት የምንላቸውን ፍረጃዎች መስፈርት ይፈልግላቸዋል።

ከዚህ ሐሳብ ጋር ስሙር በሆነ መንገድ ሐሳቡና የሚያቀርበው Shalter-Landova (2015:5) የዕሴት ምግባር ፍልስፍና ድርጊትን የሚሠሩ መርሖዎችን ለማግኜት የሚጥር ዘርፍ ነው ይላል። እነዚህ መርሖዎች ከግብረ ገብ አንጻር ትክክልና ስህተት የሆኑትን፣ ግዴታዎችንና የተፈቀዱትን ነገሮች እንዲሁም መልካሙንና እኩዩን ይነግሩናል ይላል።

በዚህ የፍልስፍና ዘርፍ ይበልጥ ትኩረት የሚሠጣቸው ፍልስፍናዊ ጥያቄዎች፡- ምንን እንዴት አድርጎ መከወን ነው ልክ? መልካም ሕይወት እንደምን ያለ ነው? ለሌሎች ያለን

የግብረ ገብ ግዴታ እስከምን ድረስ ነው? የግብረ ገብ ትክክለኝነት የሚወሰነው በምን መሥፈርት ነው? የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የግብረ ገብ ልክነት መሥፈሪያው ወይም መለኪያ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ የእለት ወይም መመሪያዊ ምግባር ፍልስፍና (Normative Ethcs) ዋና ዋና ጽንሰ ሐሳቦች መሠረት ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ምናልባትም ተጻራሪ ምላሾችም በጥቅሉ የነገረ ግብረ ገብ (Moral Philosophy) ዋነኛ የክርክር ነጥቦች ሆነው ቀጥለዋል፡፡

በተግባራዊ አንድምታቸውም በግለሰባዊም ይሁን በሀገራዊ ፖሊሲዎች ውስጥ የአንዱ ወይም የሌላው ንድፈ ሐሳብ (Theory) ገንኖ መውጣት የየራሱ የሆነ ልዩ ልዩ የግለሰብ ሕይወት እና ሀገራዊ ፖሊሲን ሲቀርጽ ኖሯል፡፡

ከየእለት (መመሪያዊ) ሥነ ምግባር ፍልስፍና ተቃራኒና ተነጻጻሪ የሆኑ ንዑሳን ዘርፎች አሉበት፡፡ ለምሳሌ አንዳንዶቹ ለሌሎች ግዴታ አለብን ሲሉ ሌሎች ደግሞ ግዴታ ያለብን የራሳችን ጥቅም ለማስጠበቅ ነው ይላሉ፡፡ በዝርዝር እንዬው፡፡

**ኃላፊነት ተኮር (Deontology)**

ይህ ጽንሰ ሐሳብ ትኩረቱ የግብረ ገብ መሥፈሪያ (መለኪያ) ድርጊቱ በሚያስገኘው ውጤት ላይ ሳይሆን ድርጊቱ ራሱ በሆነበት ትክክለኝነት ላይ ነው፡፡ እንደዚህ ጽንሰ ሐሳብ አራማጆች ከሆነ የግብረ ገብ ህግጋት መሠረት ሊሆን የሚገባው በነገሮች ያልተመሰረተ ኃላፊነት (Duty) ነው፡፡

በስሜት እና ሊያስገኝ በሚችለው ጥቅምና ጉዳት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ግን የግብረ ገብ ጥያቄነቱ በራሱ አብቅቷል የሚል መደምደሚያ አላቸው፡፡ አንድ ትክክል ያልሆነ ወይም እኩይ ነገር ጥቅም የሚያስገኝ ስለሆነ ወይም ጥሩ ስሜትን የሚፈጥር በመሆኑ ብቻ ድንገት ተነሥቶ ትክክል ወይም መልካም ሊሆን አይችልም፡፡

እንዲህ ያለው ጽንሰ ሐሳብ የግብረ ገብ ትርጓሜ እስከ ጭራሽኑ ባዶ የሚያደርግ ነው ይላሉ ፈላስፎቹ፡፡ የዚህ ጽንሰ ሐሳብ ዋና አቀንቃኝ የሆነው Kant 'Ground work of metaphysics of morals' በሚለው ሥራው የሚከተለውን ይላል 'I ought never to act except in such a way that I can also will that my maxim should become a universal law' (1998:31)

የ Kant ሐሳብ ይዘት በአጭሩ ‹‹ከማደርገው ድርጊት የሚመነጨው መርህ ሁለንተናዊ መርህ (ህግ) እንዲሆን የምፈቅደው ዓይነት እስካልሆነ ድረስ ያደረግሁት ነገር ትክክል ነው ሊባል አይችልም›› የሚል ነው፡፡

የ Kantን አባባል በምሳሌ ለማዬት ቢሞከር ለምሳሌ አንድ የመዋሸት ድርጊት ትክክል ነው ማለት የምንችለው ከድርጊቱ የሚቀዳው ‹‹መዋሸት ተገቢ ነው›› የሚለው መርህ (maxim) ሁለንተናዊ ህግ (universal law) እንዲሆን መፍቀድ ስንችል ነው፡፡ ያ ማለት ሁሌም በምንም ሁኔታ ውስጥ ማንም ቢዋሽ መዋሸት ትክክል ነው ብሎ መቀበል ግዴታ ነው፡፡ ነገር ግን ይሄንን መቀብል አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን ችግሩ እነዚህ መርሖዎች ዓለማቀፋዊ ቢሆኑ በራሱ መርሆዎቹ ተግባራዊ መሆን አይችሉም፡፡ ሁሉም ሰው በህግ ደረጃ በሚዋሽበት ዓለም እምነት ጨርሶ አይኖርም፡፡ ያለ እምነት ደግሞ ውሸት ራሱ መቀጠል አይችልም፡፡

መዋሼት ሁለንተናዊ ህግ ቢሆን ውሸት የሚባለው ነገር በራሱ አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ውሼት የተመሠረተው በመደበቅ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ጽንሰ ሐሳብ በሚከተሉት ዋና ዋና መከራከሪያ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

መከራከሪያ አንድ፡ የግብረ ገብ ህግ በአመክንዮ (Reason) እንጅ በውጤት ላይ ሊመሠረት አይችልም፡፡ ይህም ማለት ከኃላፊነት የማይመነጭ የግብረ ገብ ህግ ግብረ ገባዊ እሴት (Moral worth) ሊኖረው አይችልም፡፡ Kant ከፍ ሲል በተጠቀሰው መጽሐፉ፡ '... an action done from duty has its moral work not in the purpose, but in the priniciple of volition' (1998:27) ስለዚህም አንድ ድርጊት ግብረ ገባዊ ዋጋ ሊኖረው የሚችለው ነገሩ ከተደረገበት መነሻ (ኃላፊነትን የመወጣት ፈቃድ) አንጻር እንጅ ሊያስገኝ ከሚችለው ጥቅም አንጻር አይደለም፡፡ አንድን ድርጊት ወደ ውስጥ ሳይሆን ወደ ፊት አይተን የምናደርገው ከሆነ ግብረ ገባዊ ረብነቱን ያጣና የጥቅም ስሌት ይሆናል እንደማለት ነው፡

መከራከሪያ ሁለት፡ ሌሎች ሰዎች በራሳቸው እንደ ግብ እንጅ እንደመገልገያ መሣሪያ ልንመለከት አይገባም፤ ውጤትና ስሜት ተኮር የሆነን የግብረ ገብ መርህ የምንከተል ከሆነ ምንጊዜም የውጤትና ስሜት ግጭት ስለሚኖር እኛ ለምንፈልገው ዓላማ ሌሎችን እንደመጠቀሚያ ለመውሰድ የምንገደድበት ሁኔታ ውስጥ እንገባለን፡፡ ለምሳሌ ውሼትን ምንም እንኳ ራሳችንን ወይም የሆነን አካል ለመጥቀም ብናደርገውም በሂደት የሌሎችን እውነት የማወቅ መብት እንጋፋለን፡፡ Kant ከላይ በተጠቀሰው 'Grand Work' እንዲህ ይላል 'Act in such a way that you treat humanly …. Always as the same time as an end, never merey as a means' (Ibid:47) በጥቅሉ የDeontological Ethics ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ ከምክንያት የማይመነጩና ቋሚ ያልሆኑ፣ ከግል ፍላጎትና ስሜት ነጻ ያልሆኑ የግብረ ገብ መርሆዎች ጸንተው መቆም አይችሉም የሚል ነው፡፡ ከምክንያታዊ መግፍኤ (Motive) የማይቀዱ የድርጊት መመሪያዎች የግብረ ገብ መመሪያ መሆን አይችሉም የሚል ነው፡፡

እኔያዊ ምግባር (የግል ጥቅመኝነት) (Ethical Egoism)

ኢጎያዊ (የግል ጥቅመኝነት) የጥቅማዊነት (Telelogical ethics) አንዱ ዓይነት ሲሆን የድርጊቶችን ግብረ ገባዊ ዋጋ ወይም ትክክለኝነትና ሥህተትነት መወሰኛ መርሁ የግለሰቦች ጥቅም ነው የሚል መከራከሪያ ነው። ከወል ጥቅማዊነት (utilitarianism) በተለየ የግል ጥቅማዊነት የድርጊቶችን ውጤት ጠቃሚነት እና ጎጅነት በቀጥታ ከድርጊቱ ፈጻሚ ግለሰብ ጋር ብቻ በማገናኘት ይመለከታል።

ሰዎች በተፈጥሯቸው የራሳቸውን ፍላጎት የሚያስቀድሙ ራስ ወዳድ ናቸው ከሚለው ሥነ ልቦናዊ ጥቅማዊነት (Psychological egoism) በተለየ ምግባራዊ ግላዊ ጥቅመኝነት (Ethical Egoism) ይህ የሰዎች ተፈጥሯዊ ሁኔታ የግብረ ገብ መርህ መሆን አለበት ይላል።

ስለዚህ ሰዎች በተፈጥሮ ራስ ወዳድ ናቸው ማለት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የሰው ልጅ ድርጊት የግል ፍላጎትን ያስደቀመ ራስ ወዳድነት ያለበት መሆን አለበት የሚል ሙግት ነው። በ Rachels, J. እና Rachels, S. The elements of moral philosophy የተሰኜ መጽሐፍ '….ethical egoism is a doctrine that each person ought to pursve his or her won self-interst exclusivly' (2003፡63) የሚል ሐሳብ አለ። እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን መሻት ብቻ ሊከተል ይገባል እንደማለት ነው። ስለዚህም የሰዎችን ተፈጥሮ ከማብራራት አልፎ ራስ ወዳድነት ወይም የራስን ጥቅም ከሁሉ አስቀድሞ መመልከትን የግብረ ገብ ዋጋ (Moral Worthness) መስፈሪያ አድርጎ ይመለከታል።

Ayen Rand ''The virtue of selfishness' ባለችው መጽሐፏ 'man – every man is an end in himself, not the means to the end of others' (1964፡30) ትላለች። ይህ አገላለጽ በተለይ ከመስዋዕትነት ግብረ ገብ (altruistic morality) በግልጽ የተቃርኖ ጽንፍ የሚቀመጥ ነው። Ayen Rand እንደምትለው ሁሉም ሰው በራሱ የነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ግብ ነው። ይህም ማለት ማንም ሰው ለሌሎች ግብ መዳረሻ መንገድ መሆን የለበት የሚል አቋም ነው።

ከወል ጥቅማዊነት በተለዬ ሁኔታ የብዙኃን ደስታ ወይም ጥቅም እንደ ድርጊቶች የግብረ ገባዊነት ዋጋ ሚዛን አድርጎ አይመለከትም። ይህንን ጉዳይ Henry Sidgwick ሲያብራራ 'Egoism directs me to seek my won greatest happiness; utilitarianism is, the greatset happiness of greatset number' (1874:417) ይላል።

የወል ጥቅመኝነት ለብዙኃን የበዛውን ደስታ እንድንፈልግ ሲነግረኝ ግላዊ ጥቅማዊነት ግን ለራሴ የበለጠውን ደስታ እንድሻ ይመክረኛል የሚል ሐሳብ ነው። ሰዎች ምንጊዜም አንድን ድርጊት ከመፈጸማቸው በፊት ማሰብ ያለባቸው ብቸኛ ነገር ‹የድርጊቱ ውጤት ለእኔ ደስታን ይሰጠኛል፤ ጥቅም ያስገኘኛል?›› ብለው መሆን አለበት የሚል መከራከሪያ ነው። የግላዊ ጥቅመኝነት ግብረገባዊ ፍልስፍና መከራከሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

መከራከሪያ አንድ፡ የግልን ጥቅም መሻት፣ መከተል ከምንም ይበልጥ ምክንያታዊ የሆነ የግብረ ገብ መሠረት ነው። ሰዎች የራሳቸውን ሕይወትና ትልም ማስቀደማቸው ተፈጥሯዊና ምክንያታዊ ነው። የግብረ ገብ ፍልስፍናም ከእውነታው መራቅ እስካልፈለገ ድረስ ይህንን የሰው ልጆች ተፈጥሮ መቃረን የለበትም። ከዚህ አንጻር ራስን ሕይወትና ፍላጎት በመተው ለሌሎች የሚከፈል መስዋዕትነት ኢ-ተፈጥሯዊና ኢ-ምክንያታዊ ነው። የዚህ ዓይነቱ አመክንዮ ዋነኛ አቀንቃኝ የሆነችው Ayen Rand ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፏ ላይ እንዲህ ትላለች። 'The actor must always be the beneficiary of his action and that man must act for his won rational self-interst. The achivment of his own happiness is man's highest moral purpose' (1964:30)

የ Ayen Rand መከራከሪያ ነጥብ ሰው ከራሱ ሕይወት የበለጠ ወይም የላቀ ግብ ሊኖረው አይችልም ከሚል መነሻ የቀረበ ነው። ሌሎች በሕይወቱ ዋጋ ሊሰጣቸው የሚችሉ ነገሮች ቢኖሩም እንኳ ሁሉም በእርሱ ሕይወት መቀጠልና የሕይወት ትልም ውስጥ የሚጠቀለሉ ናቸው። ስለዚህም የግብረ ገብ ጠንካራ የሆነ መሠረት ሊኖረው የሚችለው በዚህ የሰው ልጆች መሻት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ብቻ ነው። በመስዋዕትነት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ግን ዘላቂነት ያለው እና መሰረቱ የጸና ግብረገባዊነት ሊሆን አይችልም። ለማንና መቼ መስዋዕት እሆናለሁ የሚለው በራሱ በግለሰቡ መሻት ላይ የተመሰረተ ነው አለዚያም ዘፈቀዳዊ ነው የሚሆነው።

መከራከሪያ ሁለት፡ ሥነ ልቦናዊ ጥቅመኝነት (Psychological egoism) በራሱ ግላዊ ምግባራዊ ጥቅመኝነትን (Ethical Egoism) ይደግፋል። የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው የራሳቸውን መሻት ወደ መከተል የሚያዘነብሉ ከሆነ ከዚህ በተጻራሪ የሚወጡ የግብረ ገብ መርሆዎች በሙሉ ከግብዝነት (Hypocracy) የሚመነጩ ናቸው ማለት ነው። Thomas Hobbes 'Liviatan' ባለው ድርሰቱ ላይ፡'…For no man given but with intention of good to him self; because gift is voluntary and of all voluntary acts, the object is to every man his own good' (1996:209) ይላል።

ስለዚህ ለሌሎች የምናደርጋቸው መልካም ነገሮች በሙሉ ውስጣቸውን ብንመረምራቸው ለእኛ የሚያስገኙት አንዳች ዓይነት ጥቅም በመኖሩ ነው እያለን ነው። ለሌሎች በማድረግ የሚገኝ እርካታን፣ አድናቆትን ወይም ውለታ የሚያስገኘውን ጥቅም አለፍ ሲልም ሀይማኖተኞች የሆንን ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለን ለምናምን ጥሩ መደላድል እንዲሆነን በማሰብ ነው።

መከራከሪያ ሦስት፡ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት፣ ግለሰቦች በህይወታቸው በኃላፊነት እንዲወስኑ

በተጨማሪም ነጻ እና በራሳቸው የጸኑ እንዲሆኑ ያደርጋል። በተቃራኒው የመስዋዕትነት ግብረ ገብ (altruistic morality) ሰዎች የሌሎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ በተጨማሪም ጥገኛና በሌሎች ተጽኖ ስር እንዲወድቁ የሚያደርጋቸውን ሥነ ልቦናዊ ጠባይ ያላብሳቸዋል። Ayen Rand (IBID) altruism እንደሚከተለው ትገልጸዋለች። 'Altruism holds that man has no right to exist for his won sake, that serves to others is only justification of his existence' (1964:19)

በአንጻሩ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት የሰው ልጆች ስለራሳቸው ብለው እንዲኖሩ ይሞግታል። ለሌሎች መስዋዕትነት የቀረቡ ሳይሆኑ ሕይወትን የሚወድዱ ለራስ መኖርን የሚያውቁ መሆን ይኖርባቸዋል የሚል መከራከሪያ ነው። የመስዋዕትነት ግብረ ገብ ከንቱ ሕይወትንና ኢ-ምክንያታዊ አለዚያም ደግሞ የግብዝነት ተግባር ነው።

መከራከሪያ አራት፡ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነትን ሰፋ አድርገን ስናየው በሰዎች መካከል እውነተኛ ትብብርን ለመፍጠር የሚያስችል ነው። ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የራስን መሻት ለማሟላት በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ውስጥ ከሌሎች ጋር መረዳዳት ያለውን ጠቃሚነት ይረዳሉ። በዚህም ከግብዝነት ሳይሆን ከእውነተኛ ምክንያታዊ ፍላጎት የመነጨን ተግባር መተግበር፣ ትብብርን መተባበር እንዲሰፍን ያደርጋል። በ James Rachels 'Elements of moral philosophy' የተሰኜ መጽሐፍ 'Ethical egoism does not preclude helping others; if only materials that we should help them when it is in our interst to do so' (2003:64) የሚል ሐሳብ አለ። መተባበርና መረዳዳት ስለሚያስገኘው ጥቅም ሲሉ ሰዎች ወደዚያ ያዘነብላሉ የሚል ጭምቅ ሐሳብ ያዘለ ነው። እንደዚህ ያለው ለሌሎች የሚጠቅም ነገርን የማድረግ ዝንባሌ ደግሞ ከግል ጥቅም የመነጨ እንደመሆኑ መጠን ምክንያታዊ ነው። ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት ከሌሎች ጋር መኖርን፣ መተባበርን፣ የሚቃዎም ሳይሆን ይህ ኅብረት ከእውነተኛ ግለ መሻት (Self-interets) የመነጨ መሆን አለበት ነው የሚለን።

ስለዚህም ለግላዊ ጥቅማዊ ግብረገባዊነት የግብረ ገብ ዋጋ መስፈሪያው የግለሰቦች ምክንያታዊ ግላዊ ፍላጎት እናም ያንን ተከትሎ የሚያደርጓቸው ድርጊቶች ናቸው።

## ሦስት፡ የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል የተመረጡትን ልቦለድ መጻሕፍት እተነትናለሁ። የትንታኔዬ ይዘትም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚህም የመጻሕፍቱ ይዘትና የትልም አቅጣጫ፣ የዋና ገጸ ባህርያቱ ጠባያዊ ምስሎች እንዲሁም በመጽሐፎቹ ውስጥ የተንጸባረቁ ነገረ ግብረ ገብን ያማከሉ ጭብጦች ይሆናሉ። የቀረቡበት ቅደም ተከተል የደራስያኑን የስም ሆሄያት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል በመደርደር ብሎም ከመጀመሪያ ህትመት ወደ ቀጣዩ ህትመት በሚደረግ ሽግግር ነው።

### ሰባተኛው መልአክ

መጽሐፉ በ1959 ዓ.ም የተጻፈ ይሁን እንጅ መጀመሪያ በ1992 በሌሎች አርታኢዎች አርትኦት በኋላም በ2000 ዓ.ም ‹‹እንደወረደ›› በሚል ንዑስ ርእስ ታትሟል። ነገር ግን መጽሐፉ በገጽ ብዛቱ አነስተኛ ሊባል የሚችል በመሆኑ ከዚያ በኋላ ከሌሎች መጽሐፎች ጋር ተዳብሎም ታትሟል። እኔ የተጠቀምሁት በ2009 ዓ.ም በርጩቅ ከተባለ ሌላ ልቦለድ ጋር ጀርባ ጀርብ ሆኖ የታተመውን እትም ነው። አራተኛ እትም መሆኑ ተገልጽዋል። ሰባተኛው መልአክ ደራሲው በ1950ዎቹ በፈረንሳይ ሀገር ትምህርት ሊከታተል በሄደበት ጊዜ ያለፈበት ታሪክ ስለመሆኑ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ለሁለቱም መጽሐፎች መግቢያ እንዲሆን በጻፈው ሐተታ ላይ አመልክቷል። መጽሐፉ የያዘው ታሪክም ደራሲው በአንደኛ መደብ ትረካ የሚተርከው ሆኖ በፈረንሳይ ሀገር ተማሪ የነበሩ አፍላቾች ታሪክ ነው። ለዚህ ጥናት የተመረጡት ሁለቱ የስብሐት መጽሐፎች (ሰባተኛው መልአክና ትኩሳት) ተከታታይነት ያላቸው በመሆናቸው ነው። ስብሐት በሰባተኛው መልአክ መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል

‹‹ይሄ መግቢያ ለዚህ ለምታነቡት ‹‹ሰባተኛው መልአክ›› ይሁን እንጅ ከዚህ በፊት ላነበባችሁት ‹‹የተኮላሸ ወይም ‹የተበረዘ› እትምና በቅርብ ጊዜ ‹እንደወረደ› ለምናትመው ‹‹ትኩሳት›› ጭምር ያገለግላል። የሁለቱም ልቦለዶች መቼት ያው በመሆኑ። ይዘታቸው ይለያያል እንጅ›› (ገጽ 3)

በመግቢያው አስረጅነት መሰረት ‹እንደወረደ› የተባለውን እትም በተመለከተ የህትመት ቅድሚያ ያለው ሰባተኛው መልአክ ነው። ስለዚህም አስቀድሞ ለትንታኔ መምጣቱ ለዚሁ ነው። በሌላ በኩል ‹ይዘታቸው ይለያያል እንጅ› የሚለው የስብሐት ገለጻ እኔ ከምተነትነው የግብረ ገብ ፍልስፍና ጋር የሚገናኝ አይደለም። እንዲያውም ለእኔ ትንታኔ አመችነትና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው - መጻሕፍቱ።

‹‹ትኩሳት›› እና ‹‹ሰባተኛው መልአክ›› ተመሳሳይ ናቸው። በአንድ መጽሐፍ በተጠቃለሉም ነበር። ግን መሠረታዊ የሆነ ልዩነት አላቸው። አንዳቸውን የሚመራቸው የፍቅር መንፈስ … ውጤቱ አዎንታዊና አስደሳች ሌላቸውን የሚነዳቸው የጥላቻ መንፈስ … ውጤቱ አሉታዊና አሳዛኝ (ገጽ 6)

በሰባተኛው መልአክ በጥቂት ገጾች የቀረበ መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ስብሐት እንደ አንደኛ መደብ ተራኪ አንድ ገጸ ባሕርይ ነው። ደግሞ ሌሎች ገጸ ባሕርያት አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ያሲን፣ አይሪን እና አየለ ነብር ይገኙበታል። እነዚህ ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት እርስ በእርስም

ይሁን ከለሎች አስተኔ ገጸ ባሕርያት ጋር በተገናኙ ጊዜ የሚመሩባቸውን የሥነ ምግባር ዕይታዎች ፈር እየሰጠሁ አሳያሁ።

የመጽሐፉ ማጠንጠኛ ነገረ ወሲብ ነው። ሌሎች ማቅለሚያ ታሪኮች ይኑሩ እንጅ ከታሪኩ መነሻ እስከ መድረሻ ያለው የታሪክ ሰበዝ ነገረ ወሲብ ነው። ከታሪኩ ላይ እየተጨለፉ ብቅ የሚሉ ገጸ ባሕርያት ወሲባዊ ምልከታቸው፣ ፍላጎታቸው፣ ጠባያቸው እና እምነታቸው በየገጹ ይገለጣል፤ ታሪኩን ወደፊት ያራምዳል። ወሲብ የፍቅርና የጥላቻ መነሻ ሆኖ ይከሰታል።

ሰባተኛው መልእክ የምናገኘው የግብረ ገብ ዕይታ በእኔያዊ የግብረ ገብ ፍልስፍና ስር የሚወድቅ ነው። ይህ እኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ በሁለት አንብሮዎች ላይ የሚንጠለጠል ነው። የመጀመሪያው የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር መቀበል ነው። ያሲን የተባለው አንደኛው ገጸ ባሕርይ የራሱ የሆነ ማደሪያ የለውም። ሴቶችን ይወዳል፤ ሴቶችም ይወዱታል። ዛሬ አንደኛዋ ቆንጆ ጋር ያድራል፤ በነጋታው የእሷ ጓደኛ የሆነችን ይዞ ያድራል፤ እሷም ልታሳድረው ትችላለች። በያሲን የመጣ ሴቶቹ አይቀያየሙም። ሁሉንም እኩል እንደሚወዳቸው ያውቃሉ (ገጽ 16-17) ያሲን ለሥርዓት፣ ለወግ ወይም ለይሉኝታ ብሎ የሚያደርገው ነገር የለም። እርሱ የራሱን ደስታ የሚያገኝበትን መስመር ሁሉ ይከተላል። ‹‹እውነትን በመፈለግ ላይ ነው። እና እውነትን የት እንደሚፈልጋት ታውቃለህ ……. ግብረ ስጋ ውስጥ›› (ገጽ 33)

ከዋነኞቹ ገጸ ባሕርያት መኻል አይሪን አንዷ ናት። አይሪን እንግሊዛዊት ናት። የተሳለችው በጣም ቆንጆና ጥሩ ጭንቅላት ያላት ሆና ነው። እያንዳንዱን የምታደርገውን ነገር የምታደርገው እያወቀችው ነው። ነገር ግን የምታደርገው ነገር ሁሉ እሷን እስካደሰታት ብቻ ነው። ‹‹ስለምንም ነገር ደንታ የላትም። ያሰኛትን ነገር ነው የምትሠራው። ሌሊት ሰባት ሰዓት ስምንት ሰዓት ያሲን ትዝ ያላት እንደሆነ ከአልጋዋ ተነስታ ወደ ቤት ትመጣለች›› (ገጽ 18)

በተማሪ ቤት ህግ፣ ወይም በማኅበረሰብ እሳቤ ውስጥ አይደለችም፤ የምታደምጠው ውስጧን ነው። የምታደርገው ለእሷ ደስታ የሚሠጣትን ነገር ብቻ ነው።

ደስታ የሚሠጣትን ነገር ለማድረግ ወደ ኋላ የምትል አይደለችም። ተራኪው ያሲንን በቤቱ ውስጥ አስጠግቶት በደባልነት እንደሚያኖረው ይገልጻል። (ገጽ 18) አንድ እለት አይሪን እንደለመደችው በሌሊት መጣች፤ ያሲን ግን ቤት ውስጥ አልነበረም፤ ምናልባትም ሌላ ሴት ጋ ሄዷል። በብስጭት ‘I was just in the mood to make love’ የምትለው አይሪን በቀጥታ የፈለገችውን ከመናገር አልፋ ከተራኪው ጋር ወሲብ ለማድረግ እንደምትፈልግ ‹‹ግድ ያሲን መሆን የለበትም፤ ግን ከያሲን እኩል የሚችልበት ወንድ መሆን አለበት›› (ገጽ 18-19) ማለቷ ደስታን የሚሠጣት እስከሆነ ድርስ ያሻትን የምታደርግ በመሆኗ እኔያዊ የግብረ ገብ ተከታይ (Ethical Egoist) ሆና እናገኛታለን።

ተራኪው ‹‹የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር ተቀበልኩ›› የሚለው በአንድ አልጋ ላይ ሦስት ሆነው ሲዋሰቡ ካደሩ ወዲያ ነው። ያሲን ለአይሪን ከስብሐት ጋር አብራው እንድትተኛ ነገር ግን በሩን እንዳትዘጋ ይነግራታል። አይሪን የተባለችውን አደረገች። ስብሐት ከአይሪን ጋር በመዋሰብ ላይ እያለ ያሲን በር ከፍቶ ይገባል። ያለምንም ተጨማሪ ንግግር ልብሱን አውልቆ ወሲባቸውን ይቀላቀላል። ይህ ለእኔያዊ ግብረ ገብ ፍልስፍና ተከታዩ ስብሐት ‹‹የብልግና ውበት የቆሻሻነት ክብር›› ነው። ይሄንንም ተገነዘበ ተቀበለም። የ ‹‹ብልግና ውበት›› በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። አየለ ከማኅበረሰቡ ወግ አንጻር ሲያስበው ‹‹ነውር›› ሆኖበት አእምሮውን ያናወጠው ‹‹እውነት›› ለተራኪው ምንም ነበር።

እኔ ሁለታችሁም መሃል እሆን የለ? እሱም ተራውን መሃላችን መሆን ይፈልጋል። እሱ እኔ ውስጥ ሲገባ አንተ ደግሞ እሱ ውስጥ እንድትገባ ይፈልጋል ….. እሱ (ያሲን) ወንድም ሴትም ይወዳል። እኔ የምወደድ አይነት ሴት ነኝ። አንተ የምትወደድ አይነት ወንድ ነህ። ስለዚህ ሁለታችንንም ይፈልጋል። አስታውስ። እሱ እንደኔና እንዳንተ ተራ ሰው አይደለም። በእሱ አይን እፍረት ወይም ጸያፍ የሚሉት ነገር የለም (ገጽ 36-37)

አይሪን ናት በዚህ መንገድ ተራኪውን የምታግባባው። ወደ ተሻለ ‹‹ቆሻሻነት ክብር›› እየመራችው ነው። ‹‹የብልግናን ውበት›› ተገንዝቦ የተቀበለው ተራኪ ይናገራል ‹‹ያለችኝን ለሦስት ስናደርገው ታየኝ። አልቀፈፈኝም። በሀሳቤ የያሲንን ገላ አየሁት። ብዙ ጡንቻ የለውም። ጸጉር የለበትም። አነስ ያለ ውብ ገላ ነው። በሐሳቤ አቀፍኩት። አልቀፈፈኝም›› (ገጽ 37)

በሌላ በኩል አየለ ከእኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ በተቃራኒ የመጣ ገጸ ባሕርይ ነው። አየለ በማኅበረሰብ፣ በህግ፣ በደምብ፣ በይሉኝታ ጫና ውስጥ ያለ ሰው ነው። ወሲብ እየፈለገ ሴቶችን መጠየቅ ይፈራል። ‹‹አየለ ሴቶች ፊት በጣም አይናፋር ነው›› (ገጽ 15) ያነበበው ነገር ተጽዕኖ ያደርግበታል፤ የርእዮተ ዓለም ልክፍተኛ ነው። ‹‹አየለ ግን የጋለ የተናደደ ኮሙኒስት ነው›› (ገጽ 23) ኮሙኒስት የሆነውም ለኮሙኒዝም ደምቦች በመገዛቱ ነው። ተራኪው አየለን አንጻሪ አድርጎ ያመጣው ይመስላል። እንደ እኔ ባይ ገጸ ባሕርያት በውስጡ ያለውን እውነተኛ ፍላጎት ከመከተል ይልቅ ‹‹ሰው ምን ይለኛል›› የሚል ህግ ይከተላል። እኔያዊ ገጸ ባህርያቱ በታሪኩ መጨረሻ አሸናፊ ሆነው ሲቀጥሉ አየለ ተሸናፊ የሚሆነውም ደራሲው ከሚከተለው እኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ ትክክል ነው ብሎ ለመሞገት ያደረገው ይመስላል።

ትኩሳት

በትኩሳት ውስጥ ሁለት ወገን አለ፡፡ የማኅበረሰብ መለወጥ፣ የማኅበረሰብ መሻሻል የሚገደው እና የግል ደስታን መፈለግ ብቻ የሚገድደው ወገን፡፡ ሁለቱም የየራሳቸውን እውነትና እምነት እየኖሩም፣ እየተናገሩም ሙግታቸውን ያሄዳሉ፡፡ ደራሲው እሱ ያለበትን የግል ደስታ አሳዳጅ ወገን ልዝብ የተረት ዛር ሲል ይገልጸዋል፡፡ እነባህራም ያሉበትን ወገን ደግሞ ‹‹በሳጥናኤል ኮከብ የሚመራ›› ይለዋል፡፡

ልዝብ የተረት ዛሩ ያናገረውም፣ ያኖረውን ሕይወት ‹‹በነጻነት ተኑሮ፣ በነጻነት ተጽፎ፣ በነጻነት የታተመ›› (ገጽ 259-260›› ሲል ይገልጸዋል፡፡ ይህ የግል ደስታን የመሻትና የማሳደድ ‹‹የመቆሸሽ ውበት›› ፍልስፍና ሲጽፍ ይታተምልኛል ብሎ አምኖ እንዳልነበረ በዝክሩ ላይ ይጠቁማል- ስብሐት፡፡ ሊታተምልኝ ይችላል የሚል እምነት አንዳያዳብር ያደረገው ደግሞ ‹‹ግብዝነትን እንደ ግርማ›› የለበሰው ባህላችን ነው የሚል እምነት አለው፡፡

በሰባተኛው መልአክ መግቢያ ላይ ስብሐት ስለዚህች ዓለም ስሪት ያለውን አረዳድ ይገልጻል፡፡ በዚህ አረዳዱ ውስጥ ከአስር ሰዎች ስምንቱ በጎች (ተመሪዎች፣ ተነጅዎች) ናቸው፡፡ አንዱ ግድ የሌለው አንዱ ደግሞ መሪ ይሆናል ይልና መሪዎቹ ያለምን ህዝብ (በግ) በሦስት ወገን ተቧድነው ይገዙታል፣ ይገዘግዙታል፡፡ አንደኛው መንገድ እምነት (ሃይማኖት) ነው፡፡ ሁለተኛው ወታደራዊ ኃይል ሦስተኛው ደግሞ ኢኮኖሚ ነው፡፡ እነዚህ ሦስት ኃይሎች ሰዎችን የመጨቆኛ መንገዶች በመሆናቸው መሪዎች ለተመሪው ሰፊ ህዝብ የሚጠቅም ሳይሆን ለራሳቸው ለመሪዎች የሚጠቅም ህግና ሥርዓት እየሰሩ ሲፈልጉ በግብረ ገብ ሲፈልጉ በመንግሥተ ሰማያት እያመካኙ ይጨቁኑታል፡፡ ስለዚህም ትክክለኛው የግብረ ገብ ዕይታ ለማኅበረሰብ አብዮት መሰዋት ሳይሆን የግልን ጥቅም ማስጠበቅ የግል ደስታን ማሳደድ ነው የሚለውን አመክንዮ በትኩሳት ውስጥ ይበልጥ ያብራራዋል፡፡ ይህንን የግብረ ገብ ዕይታውን ያብራራበት ይህ መጽሐፉ ታትሞ ለአንባቢያን በመድረሱም ደስታውን ይገልጻል፡፡ ስለዚህም ነው እንዲህ የሚለው፡፡ ‹‹ያን ጊዜ ግብዝነትን እንደ ግርማ ሞግስ ለብሶ ‹‹ባለህበት ሂድ›› ስልት የሚንጎማለለው ባህላችን ምናልባት እርምጃውን ይቀይር ይሆናል፡፡ ምናልባት ይሆን ይሆናል (ገጽ 259)››

በሰባተኛው መልአክ ያየናቸው ዋና ዋና ገጸ ባሕርያት የእኔያዊ ግብረ ገብ ሐሳብ አንጸባራቂ ሆነው ነው፡፡ አየለን እና ሌሎች ጥቂት ገጸ ባሕርያት ከእኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ ውጭ ያለው (እሴት፣ ሥርዓት፣ መስዋዕትነት፣ እምነት) ማኅበረሰብን መሠረት ያደረገ የግብረ ገብ ዕይታ ልክ አለመሆኑን ለማንጸር ተስለዋል፡፡ በሕይወታቸው ደስታን ሲያጡ፣ በስተመጨረሻም ራስ ማጥፋትን አማራጭ ሲያደርጉ እናያለን፡፡ ይህ ውጤቱ የተገለጸበት መጽሐፍ ነው፡፡

ትኩሳትን ግን የእኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታን ሂደት እንድናይለት አድርጎ ደራሲው ይደርሳል፡፡ ሰባተኛው መልአክ ላይ ያሲን እውቀትን የሚወድ፣ የሚያውቀውም ለማወቅ ብቻ መሆኑን ነገር ግን ሕይወትን እያጠና ያለ እውነትን እየፈለገ ያለ ትጉህ መሆኑ ይነገረናል፡፡ ያሲን እውነትን እና ሕይወትን የሚፈልጋት ወሲብ ውስጥ መሆኑም ይነገረናል፤ ከዚሁ ጋር አልፎ አልፎ ብልጭ እየተደረገ የሚነገረን የያሲን ኮሙኒስትነት ነው፡፡ ያሲን ኢራናዊ ነው፤ ኢራንን ነጻ ለማውጣት ያስብ የነበረ ኮሙኒስት ነበር፤ አሁን ግን ኮሙኒስትነቱን ትቷል፡፡ ለዚህ የተሰጠው ምክንያት ‹‹ሰላማዊ ስለሆነ›› የሚል፡፡ ኮሙኒዝም ውስጥ ምን ችግር ገጠመው የሚለው ተብራቶ አናገኘውም፡፡

በትኩሳት ውስጥ ሦስት ያህል ኢራናዊያን ገጸ ባሕርያት ይመጣሉ፡፡ ልክ እንደ ያሲን ሁሉ ቀድሞ የመጣው ገጸ ባሕርይ ኢራናዊው ባህራም ይሆናል፡፡ ጀምሽድ ቀጥሎ ይመጣል፡፡ ከዚያም ማኑ ይመጣል፡፡ እነዚህ ሦስት ኢራናዊያን ከደራሲው ጋር ይገናኛሉ፡፡ የተለያየ የሕይወታቸው ገጽታም በደራሲው በኩል ይተረክልናል፡፡ የባህራምና የያሲን ሕይወት ተናባቢ መሆኑ ግን በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ቀጣዮቹን የታሪክ አንጓዎች እንመልከት

‹‹ከፈረንሳይ መንግሥት እንደኛ እስኮላርሽፕ የለውም፡፡ ከሀገሩም ገንዘብ የሚልክለት የለም›› (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 16)

‹‹ባህራም ስኮላርሽፕ የለውም፡፡ በቤቶቹ ገንዘብ ነው የመጣው፡፡ ግን ቤቶቹ ሳንቲም ከላኩለት ይኸው ስድስት ወር አለፈ፡፡ ምን እንደነካቸው አይታወቅም፡፡ ታዲያ እሱ ሳንቲም ሳያገኝ እኛ በወር 600 ፍራንክ እየበላን ከእኛ እኩል ካፌ እየገባ ይወጣል፤ ከእኛ እኩል ሲኒማ ይገባል፤ ከእኛ እኩል ፓርቲ እየመጣ ይደንሳል፤ ሴት ያሳድዳል›› (ትኩሳት ገጽ 11)

‹‹ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚያግዘው ያገኛል፡፡ ሸሚዙ ሲያረጅ አንዷ ሸሚዝ ትገዛለታለች፡፡ ጫማው ሲያልቅ ሌላዋ ጫማ ትገዛለታለች፡፡ ክረምት ገብቶ ሊበርደው ሲጀምር አንዷ ሹራቧን ትሰጠዋለች፡፡ ይቀበላል›› (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 17-18)

‹‹ከማውቃቸው ሰዎች ከአብዛኛዎቹ አምስት አስር ሃያ ፍራንክ ተበድሪያለሁ ይመስለኛል፡፡ አሁንማ ስንት ፍራንክ ከስንት ሰው እንደተበደርኩ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ሰዎቹን በቀን በቀን አገኛቸዋለሁ፡፡ በቅርብ እመልስልሃለሁ እያልኩ ነበር የተበደርኳቸው፡፡ እና ሳያቸው አፍራለሁ›› (ትኩሳት ገጽ 67)

‹‹ያሲን ግን ያለፈቃድ ፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ሲኖር አምስት

ዓመት አልፎታል። ልዩ የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠው ባእድ ሰው ፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ስራ ሊይዝ አይችልም። ያሲን ግን ሥራ በየጊዜው ይይዛል። ሁለት ሦስት ወር ይሰራና ይተወዋል›› (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 17)

‹‹ልክ አራት ሳምንት እንደሰራ ስራው አለቀ። አሰናበቱት። ቅዳሜ ነበር። ባለውለታ አለቃውን አመስግኖ ሲሰናበታት ራት ጋበዘችው። ቤቷ አመሸ። ሲያያት እርጅና አፋፍ ላይ ደርሳለች። ወንድ ካገኘች ብዙ ጊዜ ሳይሆናት አይቀርም። ከእንግዲህ ማግኘቷንም እንጃ። ሲያስብ ጊዜ እሷ ደግ ባትውልለት ኖሮ ይሄን ጊዜ በራብ ሞቶ ነበር። ሆን ብሎ ብዙ ወይን ጠጣና ሰከረ። አብሯት አደረ። (ትኩሳት ገጽ 99)

በዚህ ብቻ ገለጻ አይደለም የሁለቱ ታሪክ የሚናበበው። ወይም ሁለቱም ኢራናዊያን በመሆናቸው፤ ሁለቱም ኮሙኒስት በመሆናቸው ብቻም አይደለም የሚናበቡት። አይሪን ስለያሲን የምትሰጠው የስሜት ምስክርነትና ሲልቪ ስለባህራም የምትገልጸው የስሜት ምስክርነተም ጭምር እንጅ።

‹‹እንደ አገልጋዩ ልትቆጥረኝ ትችላለህ። እስካሁን ያገኘሁት ሰው ሁሉ ሲያገለግለኝ ነው የኖርኩት። ለወላጆቼ አንዲት ብቻ ስለሆንኩ እነሱ አገለገሉኝ። እንደምታውቀው ረጅም ቀጭን አስቀያሚ ቢጤ ነኝ። ግን እስካሁን ያወቅኋቸው ወንዶች ልክ የውበት ንግስት እንደሆንኩ ያህል ተገዝተውልኛል። አገልግለውኛል። ብቻ ምን ልበልህ፤ በሄድኩበት እንደተገለገልኩ ነው። እና አሁን ያሲንን ማገልገል ለእኔ ሕይወት በቂ ነው›› (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 38)

‹‹አልረሳውም። ልረሳው አልችልም። ልረሳው አልፈልግም። ሌሊት እመጣለሁ አልኩትና ሄጅ አልጋዬ ውስጥ ገባሁ። ልተወው ቆረጥሁ። ምናልባት አንድ ሰዓት ያህል ቆየሁ። ከዚያ በላይ ግን ልቆይ አልቻልኩም። እንደዚህ አላስችል ያለኝ እሱ ስለሆነ ብቻ ነበር ወይስ ሰው ሲገድል ስላየሁት ነበር? አላውቅም። የሆነው ሆኖ እሱ እዚያ ተጋድሞ እኔ እዚህ ሆኜ ልታገስ አልቻልኩም። ራቁቴን ወጣሁ። ሽቶ ተቀባሁ። ከመኝታዬ ወጣሁ። የእንግዳ ቤቱን መብራት አበራሁ (ትኩሳት ገጽ 208-209)

ያሲን የተራኪው የምሥጢር ጓደኛ የመሆኑን ያህል ባህራምም ለተራኪው የልብ ጓደኛ ነው። ያሲንን ተራኪው በብዙ መንገድ የሚያደንቀውን ያህል ባህራምንም ያደንቀዋል። ያሲን ብዙ አዋቂ ተደርጎ የተሳለውን ያህል ባህራምም ብዙ ምሥጢራዊ እውቀቶችን (የካራቴ፣ የስለላ፣ የመረጃ) የተማረ መሆኑ ይገለጻል። ያሲን ሴት ማጫወት የሚያውቅበትን ያህል ባህራምም ወንዶችን ያጋደለች ሴትን በእጁ አድርጓል። ያሲን እንደተኛት እያወቀ ተራኪው አይሪንን (የያሲንን ፍቅረኛ) የተኛትን ያህል ባህራም እንደተኛት እያወቀ ኒኮልን (የባህራምን ፍቅረኛ) ተራኪው ይተኛታል።

በዚህ ልክ ታሪኮቹ ተናበው ይመጡና መለያየታቸው የሚመጣው ያሲን ቀጫጫ፣ ሰውነቱ ላይ ጸጉር የሌለበት፣ ጡንቻ የሌለው ልስልስ ሲሆን ባህራም ደግሞ ጸጉራማ፣ ጡንቻ ያለው ሆነው ተስለዋል። በሌላ በኩል ያሲን ኮሙኒዝምን ቢያውቅና ቢወድም ቅሉ ኮሙኒስትነቱን የተወ ነው። ለሪቮሊዩሽን ፍላጎት የሌለው ይልቁንም ኮሙኒዝምን እንደ አንድ አዲስ ሃይማኖት የሚያይ ነው። ባህራም ግን አሁንም ኮሚኒስት፣ አሁንም ኮሚኒዝምን የሚያነብ፣ ሪቮሉዩሽን ለማሥነሳት ተግባራዊ ሥራን የሚሠራ ነው። ትኩሳት ሲጠናቀቅም ባህራም ሪቮሊዩሽን ለማሥነሳት ሃያ ሚሊዮን የኢራን ዜጎችን ለመታደግ ቆርጦ ሲነሳ ይታያል። ይህ የሁለቱ ገጸ ባሕርያት መለያየት ግን ተለያይቶ ተለያየ የማያሰኝ መሆኑን አጥኝው ያምናል። ይልቁንም ደራሲው ይሁነኝ ብሎ ያደረገው እንጅ። ባህራም ወደ ኢራን አቀና፤ ያሲንን ሆኖ ተመለሰ። አስቀድሞ በሪቮሊዩሽን ያምን ነበር፣ ነገር ግን ከኮሙኒስቶች ጋር መቀጠል አልቻለም። በትኩሳት ላይ እንደ ምናየው ባህራም ለስንት ዓመታት የደከመለትን ሪቮሊዩሽን በአንድ ምክንያት አልሳተፍም ሲል እናያለን። ‹‹ኒኮል ነፍሰ ጡር ናት፤ ልጃችንን ጥዬ አልሄድም›› በሚል ምክንያት። መልሶ ለሪቮሊዩሽን ፈቃደኛ የሆነው ጽንሱ የአንተ ሳይሆን የልዑል ሰገድ ነው የሚል ደብዳቤ ከኒኮል ሲደርሰው ነው። እናም በሰባተኛው መልአክ እውነትን ከግብረ ስጋ ውስጥ የሚፈልግ ‹‹ተመራማሪ›› ሆኖ ብቅ አለ።

### የኅሊና ደወል - በዓሉ ግርማ

የህሊና ደወል በ1966 ዓ.ም. የታተመ ልቦለድ ነው። የታሪኩ መነሻ ሱጴ ወረዳ እልቂ ማርያም ትምህርት ቤት ነው። ከአቀንቃኙ ገጸ ባሕርይ ሀዲስ ሳህሌና ጸረ አቀንቃኙ አቶ ይርጋ ዓለሙ በሚያደርጉት ክርክር ቀመስ ውይይት ታሪኩ ይጀምራል። ይህ ሁለቱን ገጸ ባሕርያት ሳያግባባ ውይይት የሚያስጀምር ነጥብ የትምህርት ቤቱ ማርጀትና በጠቅላላው እንደ ሥርዓት በቀጠሉት ውስብስብ ችግሮች ላይ ሁለቱ ገጸ ባሕርያት ያላቸው የአረዳድ ልዩነት ነው።

ሀዲስ ሳህሌ በቀጠለው ሥርዓት ስልቹ ሆነ፤ ባለው ሥርዓት መቀጠል እንደማይችል ይናገራል፤ አንዳች አዲስ ነገር መሥራት እንደሚገባ ይሞግታል፤ በዚህ ሁሉ መሃል አደገኛ ተስፋ መቁረጥ እየተጠናወተው እንደሆነ ደጋግሞ ይናገራል። በሌላኛው ጽንፍ አቶ ይርጋ ዓለሙ በነባሩ ሥርዓት ምቾት እንዳላጡ ይልቁንም አጉል መንፈራገጥ ለመላላጥ መሆኑን ደጋግመው ይናገራሉ። ሱጴን በመሰለ ገጠራማ ስፍራ ሁኖ ምቾትን መጠበቅ ሞኝነት መሆኑን ይናገራሉ። እንዲያውም ዝም አይነቅዝም የሚል አቋማቸውን ያስረዱታል

‹‹ኑሯቸው በሰባት ዓመቶች ውስጥ ተቃንቶ በማግኜታቸው የቅድስት ማርያምን ትምህርት ቤት እንደ ገጸ በረከት መመልከትና በየዓመቱም በማርያም ስም ሰንጋ ጥለው የትምህርት ቤቱን ልጆች ወላጆች የሱጴን ታላላቅ ሰዎች

ጠርተው ማብላት ከጀመሩ ቆይተዋል። አንዳንድ ጊዜ ትምህርት ቤቱን እንደ ልብ ፍቅረኛ የሚመለከቱበትም ጊዜ አለ። ‹‹በዓይኔና በገዴ የለም ዋዛ›› ይላሉ (ገጽ 41)

የአቶ ይርጋ ሙግት ይሄ ጥቅሜ አይጓደል የሚል ነው፤ የሀዲስ ሙግት ግላዊ ጥቅም አብቅቶ ለትውልድ የሚቆይ ሥራ መሥራት ይገባናል የሚል ነው። በስተመጨረሻ በብዙ ክርክር ሁለቱም ወገኖች ለየዓላማቸው ተጉዘው የሀዲስ አቋም አሸናፊ ሆኖ አዲሱን ትምህርት ቤት ሰርቶ ሲያቆም የምናይበት መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ደራሲው በዓሉ ግርማ የግብረ ገብ ጉዳዮችን ከተለያዩ አጽናፈ መነጽር ዕይታዎች በገጸ ባሕርያት በኩል እያስኬደ በትረካው በኩል እያጎላመሰ ያስነብባል። በየሀሊና ደወል ውስጥ ደጋግሞ እንደሚስተጋባው የግብረ ገብ ፍልስፍና መሠረቶቹ የሚከተሉት ቁም ነገሮችን የሚታከክ ነው።

እምነት፡ ‹‹ሰው ሲባል ሕይወቱን የሚመራበት አንድ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል›› ‹‹እምነት የሌለው ሰው በድን ነው፤ ከእንስሳ አይሻልም›› (ገጽ 122)

ኅሊና፡ ህሊና ወደ መራን መንገድ የግድ መሄድ ይኖርብናል (ገጽ 143) ‹‹ሰበብ ህሊናን መግደል የለበትም›› (ገጽ 9)

ፍቅር፡ ‹‹ከሚጮህ ናስ አንሻልም ያለ ፍቅር። ህሊናችን ያንቀላፋል ወኔያችን ይሸናል። እምነታችን ያወላውላል። እምነቱ የሚያወላውልና ራሱን ወዳድ የሆነ ትውልድ ምንጊዜም ቢሆን ህዝቡን ሊለውጠው አይችልም›› ገጽ (177)

እውቀት፡ ‹‹የፍቅር መሰላሉ እውቀት- የእውቀት መሠረቱ ደግሞ ትምህርት ቤት ነው›› (ገጽ 145)

እጅ ((ሥራ)(ተግባር))፡ ‹‹አፈወርቅ ተክሌ የሚስላቸውን ጣቶች ይመስላሉ። ውብ አለንጋ መሳይ። ግን ምን ያደርጋል። የሀሊና ዝገት ምልክት መስለው ነው የሚታዩኝ›› (ገጽ 181) ‹‹አሁንም ቢሆን እኔ የማምነው ከብዙ ምላስ በትንሽ ሥራ ነው›› (ገጽ 178) ‹‹የሰው ልጅ ካለው ታላላቅ ጸጋዎች ውስጥ አንዱ እጅ ነው። እጇን ለሥራ እንጅ ለጥፋት ዘርግቼ አላውቅም›› (ገጽ 185)

ጊዜ፡ ‹‹ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ ጊዜን ድል ለማድረግ ከመሞከር ቦዝኖ አያውቅም። ግን ጊዜን ድል ማድረግ የሚቻለው ጊዜን በማክበር ብቻ ነው። ህልውና ማለት ራሱ ጊዜ ነው-ከጊዜ ውጭ የሆነ ነገር ከዚህ አለም አይደለምና›› (ገጽ 32) ‹‹ሰው ማንነቱና ትልቅነቱ እንዲሁም ስለሌላው ያለው በጎ ፈቃድ ርህራሄና አሳብም ጭምር የሚገመተው በቀጠሮ ሰዓት አክባሪነቱ ነው›› (ገጽ 103)

**ሀዲስ**

የሀሊና ደወል ከታተመ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ በ1975 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ለንባብ የበቃ ልቦለድ መጽሐፍ ነው። እንደገናም በ2010 የታተመ ሲሆን አጥኝው የተጠቀመው ይህን የ2010 እትምን ነው።

በትልም ደረጃ ሀዲስ ከየሀሊና ደወል የተለዬ ነው ማለት ያስቸግራል። የነበሩ ታሪኮችን ለማጎላመስ፣ ለማስፋፋትና ለማጠናከር ከተደረጉት ውጭ ያን ያህልም ጉልህ ልዩነት አለ ለማለት ያስቸግራል። ይህ ሲባል ግን ሁለቱም መጻሕፍት አንድ ዓይነት ናቸው ማለት አይደለም። በየሀሊና ደወል እንደ ትውስታ የሚመጡት የሀዲስ እናት በሀዲስ ግን የታሪኩ መነሻ ሆነው በስፋት እናገኛቸዋለን። በየሀሊና ደወል እምብዛም ታሪኩን በስፋት የማናገኘው የትምህርት ሚኒስትር ዳይሬክተሩ ታፈሰ ብሩ በሀዲስ ጉልህ ድርሻ ይዞ ይመጣል። አመጣጡም የእኔያዊ (Ethical Egoism) ፍልስፍናን አራማጅ በመሆን የሀዲስ የመስዋዕትነት ፍልስፍና የበለጠ ጎልቶ እንዲታይ ለብርሃኑ ጨለማ ሆኖ ለማሳየት በሚያምች መንገድ ነው።

በሌላ በኩል በየሀሊና ደወል ውስጥ ተደፍራ፣ ተጨቁና ሙብቷ ተገፍፎ ለሴት አዳሪነት የተዳረገች ሆና የተሳለችው፣ በስተመጨረሻም ሀዲስ ን ካላገባሁ ብላ በሀሰት ምስክርነት ለዘብጥያ የዳረገችው ሸታዬ አዲስ ማንነት ይዛ እናገኛታለን።

ሸታዬ በሀዲስ ውስጥ ትሁት ሆና ተስላለች። በሀዲስ ላይ ላይ በቅናት ትንጨረጨር የነበረችው የሀሊና ደወሏ ሸታዬ እዚህ ጋ የለችም። እንዲያውም አስተዋይነት ያላት ባሳለፈችው ሕይወት የምትጸጸትና ራሷን የምትወቅስ ሆና ትመጣለች። ሸታዬ በሀዲስ ውስጥ ተደፍራ የተጣለች ብኩን ሳትሆን በውበቷ የምትመካ፣ ሌሎችን ፉንጋ ብላ የምታጣጥል ብዙ ወንዶችን በማስከተሏ የምትደሰት ሆና ተስላለች። ‹‹ቆንጆ ሴት የትም ብትሄድ እንጀራ አታጣም እየተባለ ሲነገር ትሰማ ነበር። እና ቆንጆ የወጣላት ቆንጆ ነበረች›› (ገጽ 269) ውበቷን ተማምና ከመንደሯ ለመውጣት ያነሳሳት

‹‹የውሻ ቂጣ የመሰሰሉ የመንደሯ ሴቶች አዲስ አበባ ከርመው ሲመለሱ በጥልፍ ቀሚስና በጥበብ ነጠላ ተንቆጥቁጠው በወርቅ አምባር ድሪና ጌጣጌጥ ነደው እንቁጣጣሽ መስለው ለህዳር ጊዮርጊስ ወይም ለጥር ማርያም ብቅ ሲሉ ስታይና…›› (ገጽ 270)

ሸታዬ በዚህ አኳኋን ከቤቷ ወጥታ ከመንደሯ ኮብልላ ከቀየዋ ርቃ ብትሄድም ያሰበችውን ያህል ስኬታማ አልሆነችም። ‹‹እንደ እድል ሆኖ የታወቀች ሽርሙጣ ለመሆን እንኳ አልቻለችም›› (ገጽ 270)።

በሌላ በኩል የመስዋዕትነት ግብረገባዊነት ማሳያ ሆኖ የነበረው ቶሎሳ በሀዲስ ውስጥ ያንን የመስዋዕተንት እድሉን አላገኘም። ከእርሱ ይልቅ አቶ ጣሴ ደጉ የሀዲስ የልብ ወዳጅና የዓላማ ተጋሪ ገድለው የመሰዋት እድል ይሰጣቸዋል። በየሀሊና ደወል ውስጥ ያለ ተጻራሪ መጥፎ መጥፎ ተግባራትን ያደርግ የነበረው ሃምሳ አለቃ አሸኔ

በሀዲስ ውስጥ ተጻራሪና ተገዳዳሪ አቋም ያለው ሀምሳ አለቃ ጎይቶም ይመጣለታል። ከገበሬ ወገን ዋቆ የተባለ አንድ መስዋዕትም በሀዲስ ውስጥ በታ ተሰጥቶት ይመጣል፤ በየሀሊና ደወል ብቅ ብሎ እልም የሚለው ማኦ በሀዲስ ውስጥ ሰፋ ያለ ቦታን ይዞ ይከሰታል። ከተማሩት ወገን አቶ ጣሴ ደጉ ካልተማሩት ወገን ዋቆ መስዋዕት ይሆናሉ። ከተማሩት ወገን ማኦ (ጴጥሮስ) ካልተማሩት ወገን ሽታዬ ስህተት ላይ ይወድቃሉ። ከተማሩት ወገን ታፈሰ ብሩ ካልተማሩት ወገን ቀኛዝማች በቀለ ቱጅ የገንዘብ ፍቅር ያጠቃቸዋል። ከሹመኞች ወገን ፊታውራሪ ተካ ካገልጋዮች ወገን ቶሎሳ ቅን አሳቢ ሆነው ይገለጣሉ። ከተማሩት ወገን ሀዲስ ካልተማሩት ወገን ዓይናለም ፍቅር አምላኪዎች ሆነው ይመጣሉ። ዓለማዊውን ትምህርት ከተማሩ ወገን አቶ ይርጋ መንፈሳዊ ትምህርትን ከተማሩ ወገን መምሬ መሀሪ መርህ አልባዎች ሆነው ይገኛሉ። ይህ ሁሉ መንቶ ክፍፍል በየሀሊና ደወል የተጀመረውን የመስዋዕትነት ግብረ ገባዊ ፍልስፍና በበለጠ ስፋትና በበለጠ ምልአት ለማስረዳት ነው።

### አራት፡ ንጽጽራዊ ዕይታ

#### ሀ እኔ ወይስ እኛ?

በስብሐት ስራዎች ውስጥ የምንመለከተው እኔያዊ የግብረ ገብ እይታ እኛ ከሚለው ለእኔ የሚለውን የሚመርጥ እይታ ነው። በሰባተኛው መልአክ ውስጥ ዋነኛ ገጸ ባህርይ ሆና የመጣችው አይሪን የማህበረሰቡን እየገፋች የራሳቿን ደስታ ስትፈልግ በዚህም ደስተኛ መሆኗን ስትናገር እናገኛታለን። አይሪን Ethical egoismን የምታንጸባርቅ (የምትኖር) ሴት መሆኗን ይበልጥ በአስረጅ ለመደገፍ ከመጽሐፉ ላይ እንጥቀስ።

‹‹አየሀ በኛ ስልጣኔ ይልቁንም በኔ ቤተሰብ አካባቢ ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት እንደ ሀጢአት ነው የሚታዬው። ስለዚህ ያሲንን ከማወቄ በፊት ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት ሆኖ ባይታዬኝም እንኳዋ እንደ ጥሩ መልካም ነገር አልቆጥረውም ነበር›› (ገጽ 38)

በዚህ ንግግሯ ውስጥ ለማስተዋል እንደሚቻለው አይሪን ቤተሰቧ የሚከተለውን ይሉኝታ አፍርሳ የጣለችና በእኔያዊ ፍልስፍና የተጠመቀች መሆኗን ነው። እኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ ቅድሚያ ለራስ ፍላጎት ነው፤ ይህ ደግሞ ማኅበረሰቡ ምን ይለኛል ከሚል ዕይታ የተላቀቀ ነው። ደስታን እስካስገኘች ድረስ የቤተሰተቧ እምነት ወይም ስጋት እሷን እንደማያስጨንቃት ነው የምትገልጸው። ‹‹አሁን ለኔ ግብረ ስጋ ንጹሳ ውብ ነገር ነው። የሕይወት ዳንስ ነው። በማንኛውም ዓይነት ብደንሰው እወዳለሁ። አብሮኝ የሚደንሰው ወንድ ልበ ንጹህ ይሁን እንጅ በኔ ገላ የፈለገውን ቢሠራ ደስ ይለኛል›› (ዝኒከማሁ)

ከዚህ በተቃራኒ በዓሉ ግርማ በየሀሊና ደወል ውስጥ ዋናው ገጸ ባህርይ ሀዲስ የኋላ ታሪኩን ሲያስታውስ እንደ አይሪን ቤተሰቤ በድሎ አሳደገኝ የሚል አያደርገውም። በአስተዳደግ ከሆነ አይሪን ቀብጣ ያደገች ናት፤ ነገር ግን እንደተበደለች ትቆጥረዋለች። ሀዲስ በድህነት ስላሳደጉት እናቱ ሲያስብ የሚታወሰው ሳይደርስላቸው የማለፋቸው ጸጸት እርሱን ተከትሎ ለላቀ መስዋዕትነት መዘጋጀት ነው።

የሀዲስ የመስዋዕትነት ምግባር መነሻና መድረሻን ያዘለ ነው። በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ረፍት የሚነሳውን የአደራ ድምጽ ያስታውስና ወደ ታሪኩ ይገባል።

‹‹እጅህን በተስፋ ስጠባበቅ ኖርኩ አሁንስ ታከተኝ…. በማለት እናቱ በመጨረሻ ትንፋሻቸው ያሰሙትን በውስጡ ተዳፍኖ የቆየ እሮሮ የቅድስት ማርያም ትምህርት ቤት አሰዛኝ ሁኔታ ነካክቶ እየቀሰቀሰበት ወደ ሱጴ በሮ ከመጣበት አላማ በላይ ነግሶ በህሊናው ውስጥ ደጋግሞ ማስተጋባት ረፍት ይነሳዋል.. ሀዲስ ሰህሌን›› (1966፡5)

ይህንን የአደራ ቃል የሚጠብቀው ሊድን የሚሻ አዲስ ትውልድ አለ፤ ሀዲስ የሱጴ በሩ ህጻናትን ከጨለማው ድንቁርና የማውጣት አደራ አለበት። ‹‹እጅህን በተስፋ ስጠባበቅ ቆዬሁ፤ አሁንስ ታከተኝ›› የሚለው የእናቱ ድምጸት ህሊናውን የሚሰረስረው ይህ አደራ ስላለበት ነው። በዚህ እይታ ሀዲስ እኔ ከሚለው ይልቅ እኛ የሚለውን ይመርጣል። ሀዲስ በየጊዜው የሚያስበው አስቦም የሚፈጽመው ማህበረሰብን መጥቀም የሚችል፤ የማህበረሰብን ደስታ የሚያመጣ ሥራን ነው።

‹‹የእኔ ጥሪ ሥራ ነው። መናገር አላውቅም። ያ የጥሪ ሰዓት ሲደርስ በቆራጥነት መነሳቱ ሀጢአት አይደለም። ከማፍረስ መገንባት፣ ከብዙ ምላስ ትንሽ ሥራን፣ ከበቀል ይቅርታን፣ ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከማይምነት እውቀትን እመርጣለሁ›› (ገጽ 104)

ይህ እምነቱ የፈራረሰ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አዲስ ትምህርት ቤት ለመስራት ያስችለዋል። በክፍል ጥበት ምክንያት መማር ያልቻሉ ልጆች ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የተከፉ ወላጆች ወደ ደስታ ስሜት እንዲገቡ ያደርጋል። በሰብሀት ስራዎች ውስጥ ግን የዚህ ተቃራኒ የደስታ አማራጮች ይቀርባሉ።

ሥብሐት በትኩሳት ውስጥ ‹‹ያን ሰሞን አንዲት ቆንጆ አሜሪካዊት ነበረች። አይኗ ሰማያዊ፣ ጸጉሯ በጣም ንጹህ ቡና አይነት። እጅግ ደስ ትላለች። አልጋ ውስጥ ልብ ታጠፋለች›› (ገጽ 14) በሚል ከወሲብ ጋር ያለውን ቁርኝት የሚናገረው ተራኪው ብዙ ሳይቆይ ሲልቪን ከተመስገን አለያይቶ የግብረ ስጋን ቅደስና ይተርካል። ልዑል ሰገድ ተገድሎ መቀበሩ እንኳ ሳይነገር ምናልባትም በሰዓታት ውስጥ ልኡል ሰገድን ፍለጋ ከመጣች አማንዳ ጋር ያደረገውን ወሲብ ቅድስና ይናገራል ‹‹መኖሩን ሰምቸው የማላውቀው አዲስ የግብረ ስጋ አገር አሳየችኝ›› (ገጽ 225)

ይላል። ሲልቪ የተመስገን፣ አማንዳ የልኡል ሰገድ ፍቅረኞች ነበሩ። የቀረችው የባህራም ፍቅረኛ ኒኮል ነበረች። ኒኮል የባህራም ፍቅረኛ ትሁን እንጅ ልዑል ሰገደም ጀምሽድም ደጋግመው ተኝተዋታል፤ እንዲያውም ተጋድለውባታል። ይሄኛውን የመደምደሚያ አድርጎ ያመጣውና እንደ ያሲን ቅዱሥነትን ያብራራል

‹‹….ያች ልጅ መንግስተ ሰማያትን አጣጥፋ ጠቅላ በጭኖቿ ውስጥ ደብቃ ነው የምትዞረው ልልህ እችላለሁ። እኔ ምለው እንደ ኒኮል ያለች ሴት እየተኙ ሁለት አመት ኖረው ቢሞቱ ምናለበት? ቢሰነብቱ ትርፉ ማርጀት አይደለም? እርጅና መጥቶ አጥንቶቼን አኮራምቶ ጅማቶቼን ሸምቀቆ፣ ቆዳዬን አጨማዶ፣ አይኔን አጨናብሶ፣ ጠረኔን ሰርቆ፣ በቁሜ በኤክስ አሮጊቶችና ሽማግሎች ሽታ ከሚገንዘኝ ኒኮልዬ ጭኖች መሃል ገብቼ ሙቀቱ ውስጥ ቀልጬ፣ ርጥበቱ ውስጥ ሟሙቼ ጥፍት ብል እመርጣለሁ። የሰው ልጅ መጨረሻውን መምረጥ ቢችል፣ መጨረሻዬ ኒኮል ውስጥ ቢሆንልኝ እመርጣለሁ…›› (ገጽ 253)

በሁለቱም መጽሐፎች ውስጥ ሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር የተከተለው የግብረ ገብ ፍልስፍና ‹‹እኔያዊ›› (Ethical Egoism) የሚባለው ነው። በጠቅላላው የስብሀት ትኩረት የግል ደስታን ሲያጥጥሙ ኖሮ ማለፍ ነው።

ለበዓሉ ግን ምግባር የዚህ ተቃራኒ ነው። በሀዲስ ውስጥ ሀዲስ በእምነትና አቋሙ፣ በተግባርና አመለካከቱ ለምን እንደመጣ እንደሚያውቅ ሲያሳይ ለማየት ይቻላል። ይህንም ሲያደርግ ከላይ ያነሳናቸውን ለፍልስፍናው መሠረት የሆኑትን አስተምህሮዎች ወደፊት በማምጣት ነው። አስረጅ እንጥቀስ። በአንድ ወቅት ለተማሪዎቹ አንድ ጥያቄ ያነሳል። ‹‹ነጻነቱን የሚያከብርና የሚወድ ማን ነው?›› (ገጽ 256)

ተማሪዎችን ድንገት ነው ይህን ጥያቄ ያነሳባቸው። ተማሪዎቹ መልስ ይሆናል ያሉትን ሁሉ ሙከራ ይሞክራሉ። ሀዲስ ይቀጥላል

እሽ ልጆች ጥሩ ነው። ግን እኔ ያሰብኩትን መልስ አላገኛችሁትም። ነጻነቱን የሚወድና የሚያከብር ሰው ማን ነው? ብትሉኝ እኔ የምሰጠው መልስ ግዴታውን አውቆ የሚያከብር ሰው ነው የሚል ይሆናል። ለምን ብትሉኝ ግዴታውን የማያውቅ ሰው ነጻነቱን ያውቃል ወይም ያከብራል - ለነጻነቱ ይታገላል ወይም ይሞታል ብዬ ስላማላምን ነው። ሕይወት ራሷ የግዴታዎች ሰንሰለት ናት። እና ግዴታውን አውቆ የሚያከብር ሰው ምንንጊዜም ለማንም ባርያ ሆኖ አይኖርም (ገጽ 256)።

በዚህ የሀዲስ ንግግር ውስጥ ቁም ነገሮችን እናገኛለን። አንድ ሰው ነጻ ካልሆነ በቀር ግፍን ሊቋቋምና ሊከላከል የሚችልበት ብቃት ሊኖረው እንደማይችል ከፍ ባለው ትንታኔ የተመለከትንለት ሀዲስ ወዲህ ደግሞ ነጻነቱን የሚያውቅና የሚያከብር ሰው ለመስዋዕትነት ዝግጁ ይሆናል ይላል። ለብዙሃኑ ደስታ ሲባል መስዋዕት መሆን ደግሞ የሕይወት ግዴታ ነው - ለሀዲስ። ግፍን ለመቋቋም ካለመስዋዕትነት በቀር ሊሆን አይችልምና። ለዚያ ነው ሀዲስ ‹‹በፈሪና በጀግና መካከል ያለው ልዩነት ፈሪ ሲሸሽ ጀግና ሲታገል የሞታቸው ጉዳይ ነው›› (ገጽ 79)። የሚለው። ጀግና ለመስዋዕትነት ፊት ለፊት ይጋፈጣል፤ ፈሪ ለማምለጥ ሲል ከጀርባው ይመታል።

## ለ ፍቅር ወይስ ቅንዝር?

የሁለቱን ደራስያን የግብረ ገብ እይታ ልዩነቶች ከምናይባቸው ጉዳዮች ‹‹ፍቅር›› የሚባለው ጽንሰ ሐሳብ ላይ ባላቸውን ምልከታ ነው። በስብሐት ስራዎች ውስጥ ፍቅር በመቆሸሽ፣ በመባለግ ውስጥ የሚገኝ ነው። በሰባተኛው መላክ እንዲህ ይላል ስብሐት

‹‹በህይወቴ እንደዚያች ያለች ሌሊት አሳልፌ አላውቅም። የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር ለመጀመሪያ ጊዜ መገንዘቤና መቀበሌ ነበር›› (ገጽ 21)

በትኩሳት ውስጥ ደግሞ ሲልቪ በተደጋጋሚ ወንዶችን እያየች ያየቻቸውንም እየተመኘች ከተራኪው ጋር ትተኛለች። ታዲያ ‹‹የቆሻሻነትን ክብር›› የሚወደው ተራኪው ከዚህ ውስጥ ደስታውን ሲፈልግና ሲያገኝ ያሳየናል። ከእሱ ጋር ተኝታ ከሌላ ወንድ ጋር በሃሳብ ስትገናኝ ‹‹አልቀፈፈውም›› እንዲያውም ይበልጥ ደስታን እየሰጠው መጣ እንጅ ‹‹ከንፈሯ በሚያስጎመጅ አኳኋን ይርበተበታል (ምኞቱ ሲያሳብጠኝ ተሰማኝ። ታዲያ ከፍርሃት ጋር ነው። ምክንያም የተመኘኋት ቆንጆ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን ሰውየውን ስትመኘው ስላየኋም ነው?)›› (ገጽ 88)

ይቀጥልና ተራኪው በሚሰሩት የብልግና ሥራ ውስጥ የበለጠ ደስታን እያገኘ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ከብልግና ላይ የሚገኝ ደስታ ‹‹እኔያዊ›› እንጅ ባህልን፣ ሃይማኖትን ወይም ሌላ ዓይነት ደንብና ሥርዓትን ያማከለ አይደለም። እንዲያውም በደምብና በሥርዓቶች ላይ ያመጸ እንጅ። ተራኪው የቆሻሻነትን ክብር ይገልጸዋል።

‹‹ተቃቀፍን። እንደ አንድ ቀኑ ሌሊት ተንገበገበች። ስስማት አፌ ውስጥ እያቃሰተች ጭኖቿን ከመጠን በላይ ፍርክክ አድርጋ አቀፈችኝ። ደምበኛው ፍቅር ሳይሆን ቆሻሻ ብልግና የምንሰራ መስሎ ተሰማኝ። የባሰ ቆሻሻ እንዲሆን አማረኝ›› (ገጽ 88)

በርግጥ የበለጠውን ‹‹ደስታ›› ለማግኘት የባሰ ቆሻሻ እየሆነ ሲሄድ ተራኪው ያሳየናል። በሀሳቧ ሌሎች ወንዶችን እያሰበች ከእሱ ጋር ትተኛ ከነበረችው ሲልቪ ጋር የበለጠ ቆሻሻ ለመሆን ይመክራሉ።

የበለጠ ደስታን ፈለጉ፣ እናም በውስጧ የሚሰማትን እና የምትፈልገውን የደስታ ዓይነት ነገረችው። ከእሱ ጋር ከመተኛቷ በፊት ከሌሎች ሦስት አራት ወንዶች ጋር መተኛት እንደምትፈልግ ትነግረዋለች (ገጽ 191) አልከለከላትም። ከአራት ወንዶች ጋር እድትተኛ ይልካታል፤ ታዲያ ከዚያ ስትመጣ ደግሞ ከእሱ ጋር እንደምትተኛ ያውቃሉ። ይሄንን የዋጋ አጣብቂኝ (Value Stuck) ፈትቶ ያሳየበት የስብሐት የግብረ ገብ ፍልስፍና ሆኖ በአጥኝው ዐይን ታይቷል። እነሆ አጣብቂኙ

‹‹የሚያፈቅሯት ሴት ጥብቅ ያለ ሱሪ ለብሳ ሌላ ወንድ ፍለጋ ስትሄድ ማየት፣ ሄዳ ስትመለስ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ወንድ በየተራ ሲደስትባት፣ ሲስማት፣ ሲልሳት፣ ሲያለፋት ከቆየ በኋላ  ከዚያ ተቀብለው ይሄንን ሁሉ እያወቁ ያችን የሚወዷትን ሴት ማቀፍ፣ መሳም፣ መላስ፣ በቅናት እየነደዱ ሴትዮዋን መተኛት - ይሄ ደግሞ ከሁሉ የጠለቀ፣ ከሁሉ የላቀ፣ ከሁሉ የደመቀ፣ ከሁሉ የጨለመ፣ የሚያቃጥል፣ የሚያበርድ፣ የሚያስደስት፣ የሚያበሳጭ፣ የሚገድል፣ የሚያድን፣ ከስሜት በላይ የሆነ ስሜት ይሰጥ ይሆን›› (ገጽ 191-192)

ይሄ ለቅጽበት ያመጣው የግብረ ገብ አጣብቂኝ ጥቂት ጊዜ ከእርሱ ጋር ይቆያል። ሲኒማ ገብቶ ፊልም አይቶ እስኪወጣ ድረስ ግን ተመልሶ በአእምሮው ሲመጣበት አልነገረንም። እንዲያውም ጉዳዩን ረስቶት እንደነበር ያነሳል። በውላቸው መሠረት ሲልቪ ከአራት ወንዶች ጋር ተኝታ ከቀጠሮ ሰዓቷ አርፍዳ ትመጣለች፡ እንደ አመጣጧ ተቀበላት እናም እንዲህ ይላል

‹‹ነገረችኝ። የሳሟትን፣ የላሷትን፣ የነከሷትን፣ ሁሉን አንድ ባንድ ነገረችኝ። የስሜቱ አዲሥነት፣ ብዛት፣ ጥልቀትና ኃይል ካሰብኩት በላይ ሆነ። መጨረሻ ላይ ከስሜት ብዛት ስጮህ በእጇ አፌን አፈነች። በብዙ ለስላሳ ቃላት ‹አይዞህ ያንተ ነኝ›› እያለች አባበለችኝ። ገና ከላይዋ ሳልወርድ እንቅልፍ ወሰደኝ›› (ገጽ 195)

ይህ የበለጠ የመቆሸሽ ፍላጎት በፍላጎት ብቻ ሲቀር አይታይም። እንዲያውም ይበልጥ እየቆሸሸ ይበልጥ ብልግናው እየጨመረ ‹‹የብልግና ውበቱም›› ይበልጥ እየፈካ ሲሄድ እናያለን።

በዓሉ ለፍቅር የሚሠጠው ትርጓሜ ግን ሌላ ነው። ፍቅር ለማህበረሰብ የሚሰጥ በረከት ነው። ይህ በረከትም እጅን (ተግባርን) የሚጠይቅ መስዋዕትነትንም ሊያስከትል የሚችል ነው። በየህሊና ደወል ውስጥ በገጽ 111  እንዲህ ይላል

‹‹ታዲያ ወደፊት  ልንራመድ የምንችለው በወሬ-በፍልስፍና-በሥራ በማይገለጥ የመጽሐፍ እውቀት አይደለም። ሥርየታችን ሥራ ነው። ማህሌት ቆሞ በማደር፤ ቤተመቅደስን በማጠን -በጾም በጸሎት ብቻ አይደለም። ሥልጣን ይዞ በመኮፈስ-ስልጣንን እንደ እውቀት በመቁጠር - ስልጣንን እንደ አላፊነት ሳይሆን እንደ መብት በማዬት አይደለም። በስልጣን ሰገነት ላይ ወጥቶ ከህዝብ ትንፋሽ በመራቅ እንደ ኮከብ እያንጸባረቁ በመቀመጥ- የህዝብ እንባ ከማይደርስበት ቦታ - በሥራ እንደገና መወለድ ያስፈልጋል። የዘመኑ ጀግና ሰራተኛ ነው። ሥራ ስሩ ብሎ መለፈፍ ብቻ አይበቃም። ሰርቶ ማሳየት ያስፈልጋል። ትችት ብቻውን የአእምሮ መካንነት-የወኔ ማጣት ምልክት ነው።

ሰው በህሊናው ያሰበውን መልካም ይሁን መጥፎ የሚተገብረው በእጁ ነው። እጅ የመጨረሻው ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖ ነው የቀረበው። ሀዲስ፣ ፊታውራሪ ተካና እነ ቶሎሳ የሚያራምዱት የበጎ ምግባር መገለጫ መልኮችን ነው። ሀዲስ ከዚህ በላይ ያለውን ንግግር ሲያደርግ የመልካምነት መገለጫው ተግባር እንጅ ቃላዊ መነበንብ አመሆኑን እየሞገተ ነው።

የእኔ ጥሪ ሥራ ነው። መናገር አላውቅም። ያ የጥሪ ሰዓት ሲደርስ በቆራጥነት መነሳቱ ሀጢአት አይደለም። ከማፍረስ መገንባት፣ ከብዙ ምላስ ትንሽ ሥራን፣ ከበቀል ይቅርታን፣ ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከማይምነት እውቀትን እመርጣለሁ (ገጽ 104)

ይህ የመልካም ምግባር መለኪያ መሆኑን ያስረዳል። ሀዲስ ህሊናውን በእምነት ፍቅሩን በእውቀት ያነጸ ወይም ማነጽ የሚፈልግ መሆኑን ይገናራል። ‹አውቃለሁ›› ብሎ ከመናገር ወይም ‹‹ያውቃል›› ተብሎ ከሚነገርለት ይልቅ በእጁ መሥራትን እንደሚመርጥ ይናገራል። አንድ ሰው ጥሩ ትምህርት ያለው መሆኑ የሚታወቀው የተማረውን በእጁ መሥራት ሲችል ነው፤ ቃል በቃል ቢያነበንበው ልክ አይደለም የሚል አቋም አለው ሀዲስ ። በሀዲስ ውስጥ ለመስዋዕትነት ዝግጁ መሆኑን የሚያስረግጠው በዚህ መልኩ ነው

‹‹አንዳንድ ምቀኞች በሚያውጠነጥኑት ሴራ መሸበር ለብንም። የተነሳሳነው ለበጎ አላማ እስከሆነ ድረስ ቆርጠን መስራት አለብን። ኣላማ ያለው ሰው እስራት፣ ግርፋት፣ ርሃብ ስቃይ ወይም ሞት ምኑም አይደሉም። ከመሞታችን በፊት አስሬ መሞት የለብንም። ኤጭ! ምንድን ነው የሚያስፈራን! ድምቢጥ እንኳ ካቅሟ ልብ አላት። ሀተታ አላበዛም። (ገጽ 121)።

ይህ ሁሉ የሚሆነው የብዙሃኑን ደስታ ለማስግኜት ሲባል ነው። ሀዲስ ምኞቱን፣ ድሎቱን፣ የግል ደስታውን በመተው የብዙሃኑን ደስታ ሊፈጥር ሲጣጣር የስብሀት ገጸ ባህርያት ግን  የግል ደስታቸውን ‹‹ቆሻሻነት ውስጥ›› ሲያስሱ እናያለን። ይህ በሁለቱ ደራስያን መካከል ያለ የግብረ ገብ እይታ ተቃርኖ ነው።

**አምስት፡ ማጠቃለያ**

የተመረጡት ልቦለዳዊ ሥራዎች ናቸው። ስብሐት ግብረ

እግዚአብሔር በማስታወሻው ላይ እንደገለጸው በፈረንሳይ ሀገር ተማሪ በነበረበት ጊዜ ያሳለፈውን የአፍላኝነት ጊዜ ነው የጻፈው። ያም እውነትን የተመሰረተ ታሪክ ስለመሆኑ ይገልጻል። በዓሉ ግርማ ተወልዶ ያደገበትን አካባቢ ነው የጻፈው፤ ከሚያውቀው ካደገበት ለመጻፍ አንደቻለ መረዳት ይቻላል። እነዚህ መጽሐፎች የእውነተኛ ታሪክ ነጸብራቆች ስለሆኑ ደራስያኑ ያንን እውነት ታክከው የሚያቀርቡት ትነታኔ የየደራስያኑን የምግባር እይታዎች ያሳያል በሚል መላ ምት ትንታኔው ተሰርቷል። በሁሉም መጽሐፎች ለማየት እንደተቻለው በመጀመሪያዎቹ መጽሐፎች ይዘው የተነሷቸውን የምግባር መከራከሪያዎች በሁለተኛ መጽሐፎቻቸው የበለጠ አብራርተውና አስፍተው ጽፈው ተገኝተዋል።

የዚህ ጥናት ግኝት ደራስያኑ የምግባር ፈላስፎች ናቸው ወይም በጠቅላላው ፈላስፎች ናቸው የሚል አይደለም። ይልቁንም በሥራዎቻቸው ውስጥ ፍልስፍናዊ ይዘቶች አሏቸው የሚል እንጅ። በዚህም መሠረት ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር የእኔያዊ የምግባር ፍልስፍና አቀንቃኝ ነው የሚያሰኝ ግኝት ተገኝቷል። በመቆሸሽና በብልግና ውስጥ ያለውን ውበትና ክብር በመጽሐፎቹ ተርኳል። ይህ ግላዊ ነው። በሃይማኖት፣ በማኅበረሰብ፣ በባህል የሚመሩ ወይም በእነዚህ ውስጥ ያደጉ እሴት አክባሪዎች ከመቆሸሽ ውስጥ ክብርን ከብልግና ውስጥ ውበትን የሚፈልጉ አይደሉም። ወይም ይሄንን የሚያደርግን ሰው እንደ ጤነኛ አይመለከቱም።

በምግባር ፍልስፍና ውስጥ ግን ይሄ አንደኛው የግብረ ገብ እይታ ተደርጎ ይወሰዳል። አንድ ሰው የፈለገውን፣ ደስታ የሚፈጥርለትን ነገር የማድረግ ስልጣን አለው ከሚለው ጀምሮ እንዲያውም ይሄንን ማድረጉ ትክክል ነው የሚለው የምግባር ፍልስፍና እኔያዊ (Ethical egoism) ነው። ይህ የሥብሐት መገለጫ ስለመሆኑ በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

በዓሉ ግርማ በሁለቱም መጽሐፎች ውስጥ ያስነበበን የግብረ ገብ ዕይታ የስብሐት ተቃራኒ ነው። የስብሐት ገጸ ባሕርያት እኔ የሚሉ እና ለግል ደስታ የሚነሱ ናቸው። የበዓሉ ገጸ በህርይ ግን እኛ የሚልን ለብዙሃኑ ደስታ የሚነሳ ነው። በየህሊና ደወልና በሀዲስ ውስጥ ዋናው ገጸ ባሕርይ ሀዲስ ሳህሌ ከግል ደስታና ጥቅሙ ይልቅ ለብዙሃኑ ደስታና ጥቅም ሲነሳ እናያለን። መነሳት ብቻ ሳይሆን መስዋዕትነትም ሲከፍል እናያለን። ይህ እኔያዊ (Ethical egoism) ተቃራኒ የሆነው የመስዋዕትነት (Altruistic Morality) መገለጫ ስለመሆኑ በጥናቱ መረጋገጥ ተችሏል።

እነዚህ ሁለት ደራስያን ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ በርካታ አንባቢያንን ማፍራት ችለዋል። ሥራዎቻቸውም በማኅበረሰብ ዘንድ የየራሱ የሆነ ሚና እና ተጽዕኖ አሳርፏል። በአንድ በኩል ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርንና ሥራዎቹን የሚያወግዝና የሚኮንን አለ፤ በሌላ በኩል የስብሐትን ስራዎች አርአያ አድርጎ የሚጽፍ ጸሐፊና የስብሐትን ሕይወት ምሳሌ አድርጎ ለህይወት ደንታ ቢስነተን የሚለማመድ አለ። ይህ ጥናት ስብሐት የእኔያዊ ፍልስፍና አራማጅ እንደነበረ ሥራዎቹም የእኔያዊ ፍልስፍና ማራመጃ እንደነበሩ አረጋግጧል። ሌሎች አጥኝዎች ይህ የስብሐት እኔያዊ የግብረ ገብ ዕይታ በአሁኑ ትውልድ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ይኖር ይሆን ብለው ቢያጠኑ ይሄ ጥናት መሰረት ይሆናቸዋል።

በሌላ በኩል በዓሉ ግርማ በሁለቱም መጽሐፉቹ ያንጸባረቀው የመስዋዕትነት ግብረ ገብ ዕይታ በተለይ በአብዮቱ ትውልድ በጣም ተነባቢ እንዲሆን አድርጎታል። አሁን በተግባር የምናያት ኢትዮጵያ ደግሞ የአብዮታዊያኑ (ስልሳዎቹ) ትውልድ አባላት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የፈጠሯትና የሚመሯት ናት። በመሆኑም ሌሎች አጥኝዎች አሁን ያለንበት ሁለንተናዊ የግብረ ገብ አጣብቂኝ እና የበዓሉ ግርማ ተጽእኖን ቢያጠኑ ይህ ጥናት መነሻ ይሆናል።

## ማጣቀሻዎች

### አንደኛ ደረጃ ምንጭ


ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር (2012) ትኩሳት፡ 11ኛ ዕትም፤ ወይንሸት ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

__________________ (2009) ሰባተኛው መልአክ፡ አራተኛ እትም፤__________________

በዓሉ ግርማ (2005) የህሊና ደወል 3ኛ እትም ማንኩሳ አሳታሚ ድርጅት፣ ማንኩሳ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ

__________________ ሀዲስ3ኛ እትም ማንኩሳ አሳታሚ ድርጅት፣ ማንኩሳ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ


### ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች


ሰላማዊት በየነ፣ የተፈጥሮና ባህል ግጭትና እርቅ በአዳም ረታ ህማማትና በገና (ያልታተመ)፣ የአምርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2010።

ኤሊያስ አያልነህ፣ ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖብል፣ አርቲስክ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ በባ፣ ኢትዮጵያ፣ 2000።

ጠና ጠና ደዎ ሰው ግብረገብና ሥነ ግበረ ገብ ፡ የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ፣ 2008።

ደሳለኝ ሥዩም፣ የፍልስፍና መግቢያ፡ በሀገርኛ ቋንቋ፣ ለታሪክ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ 2014።

ብሩህ ዓለም ነህ፣ የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ የዘርዓ ያዕቆብ ና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ ________________ አዲስ አበባ፣ ኢትጵያ፣ 2009

የማነ ገ/ማርያም የፍልስፍና መግቢያ ቅጽ አንድ፣ ሰዋሰው ብርሀን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አዲስ አበባ፣ 1996።

Bernstein J.M (1992) The fate of Art: aesthetic alienation from Kant to Derrida and Adorno, the Pennsylvania state university press, USA

Sidgwick, H. (1874). The Methods of Ethics (7th ed.). Macmillan.

Hobbes, T. (1996). Leviathan (R. Tuck, Ed.). Cambridge University Press. (Original work published 1651.

Kant, I. (1998). Groundwork of the metaphysics of morals (M. J. Gregor, Trans.). Cambridge University Press.

Moran J. (2002) Interdisciplinarity, published by Routledge, London and NewYork

Plato v. Disputatio, Vol. XIII, No. 62, December 2021 ©2021 Schiller on the Aesthetic Constitution of Moral Virtue and the Justification of Aesthetic Obligations,. Creative Commons Attribution-Noncommercial-No Derivs 3.0 License

Rand A (1964) 'The virtue of selfishness ; a new concept of egoism, Signet book, New American Library, New York.

Rachels, J., & Rachels, S. (2003). The elements of moral philosophy (5th ed.). McGraw-Hill.

Rosalind Hursthouge, 1998, Virtue Ethics, Stanford encyclopedia of Philosophy (online published)

Shafer-Landau, R. (2015). The fundamentals of ethics (3rd ed.). Oxford University Press.)

Sidgwick, H. (1874). The Methods of Ethics (7th ed.). Macmillan. p. 417. )

Tena S. (2008) Unpublished, The changing face of moral vision in Amharic novel, Ph.D dissertation, English Literature AAU.

William F. (1973). Ethics (2nd ed.). Englewood Clif